የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለአራተኛ ክፍል



በአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ፍኖተ ብርሃን ሰንበት ት/ቤት ትምህርትና ስልጠና ክፍል የተዘጋጀ

ምዕራፍ አንድ

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አመሰራረት

ምዕራፍ ሁለት

በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ የሚገኙ ታሪካዊ ገዳማት ማሳያ

2.1. ደብረ ዳሞ አመሰራረቱ

2.2. አክሱም ጽዮን ማርያም

2.3. ደብረ ማርያም

2.4. አቡነ ይምአታ

2.5. አባ ጸንጠሌዎን

2.6. ማኅበረ ዶጌ

ምዕራፍ ሦስት

በጎንደር የሚገኙ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያት ማሳያ

3.1. ጎንደር ቅድስት ሥላሴ

3.2. ዙር አምባ

3.3. ዋሻ እንድርያስ

3.4. ዋሻ ተክለ ሃይማኖት

ምዕራፍ አራት

በወሎ የሚገኙ አድባራት እና ገዳማት

4.1. ላሊበላ ውቅር አብያ ክርስቲያናት

4.2. ግሸን ደብረ ከርቤ

4.3. ብልብላ ጊዮርጊስ

4.4. ይምርሐነ ክርስቶስ

ምዕራፍ አምስት

ጎጃም ባህርዳርና ዙሪያዋ የሚገኙ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያት ማሳያ

5.1. ጣና ሐይቅ ገዳማት

5.2. መርጦለ ለማርያም

5.3. ደብረ ወርቅ ማርያም

ምዕራፍ ስድስት

ሸዋ እና ዙሪያዋ የሚገኙ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያት ማሳያ

6.1. ደብረ ብርሃን ሥላሴ

6.2. ቅድስት ክርስቶስ ሰምራ

6.3. ደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት

ምዕራፍ ሰባት

ምዕራብና ምስራቅ ደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ጥንታውያን አድባት እና ገዳማት ማሳያ

7.1. ቁልቢ ገብርኤል

7.2. አዲስ አለም ማርያም

7.3. አዳዲ ማርያም

7.4. ብርብር ማርያም

ምዕራፍ አንድ

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አመሰራረት

- ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት መጀመሪያ በህገ ልቦና በመቀጠለም በሕገ ኦሪት እግዚአብሔርን ስታመልክ የኖረች ሀገር መሆኗን የሚታወቅ ነው፡፡ በበሉይ ኪዳን መሐፍ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በቡዙ ቦታዎች ላይ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡
- ኢትዮጵያ ከህገ ልቦና ወደ ህገ ኦሪት ከህገ ኦሪት ወደ ህገ ወንጌል የተሸጋገረችበት ሁለት ታሪካዊ ሂደቶች አሉ:: የእግዚአብሔር ፍቃድ ሆኖ እነዚህ ሁለቱ ታሪካዊ ሂደቶች ተመሳሳይነት አላቸው ፡፡ ከአክሱም ወደ ኢየሩሳሌም የተደረጉ ጉዞዎች ናቸው፡፡
  - ✓ **አንደኛው** የንግስት ሳባ ጉዞ ሲሆን
  - ✓ **ሁለተኛው** የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የቅዱስ ባኮስ ጉዞ ነው፡፡

ታሪካዊ የጉዞ	የንግስት ሳባ (ማክዳ)	የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ
የጉዞው መነሻ	አክሱም	አክሱም
የጉዞው መድረሻ	ኢየሩሳሌም	ኢየሩሳሌም
የጉዞው ጊዜ	ቅ/ል/ክ 1000 ዓመት አካባቢ	በ34 ዓ/ም ከክርስቶስ ዕርገት 1 ዓመት በኃላ
የተጋገሮች ማንነት	የኢትዮጵያ ንግስት	የንግስት ህንደኬ በጅሮንድ
የጉዞው ምክንያት	የንጉስ ሰለሞንን ጥበብ ለማየት፣ ለመፈተን የሰራቸውን ታላላቅ ስራዎች ለማየት	ኢየሩሳሌምን ለመሳለም በእስራኤል ያሉን ግዛቶች ለማየት ለመምራት

ሲመለሱ	ቀዳማዊ ምንሊክን ጸንሳ ተመለሰች ቀዳማዊ ምንሊክ ደግሞ ታቦተ ጽዮንን፣ ሥርዓተ ኦሪትንና ካህናተ ኦሪትን ይዞ መጣ	በቅዱስ ፊልጶስ እጅ ተጠምቆ ሃብተ ውልድናን ክርስትናን ቅዱሳት መጽሐፍትን የክርስትናን የምስራች ዜና
ውጤት	ከህገ ልቦና ወደ ህገ ኦሪት	ከህገ ኦሪት ወደ ህገ ወንጌል
ምንጭ	1ኛ ነገ 10	የሐዋ ሥራ 8

- በሃገራችን በርካታ ጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያን ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ቤተ-ክርስቲያን ደግሞ እጅግ ብዙ አስደናቂ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህል
  - ✓ በሥርዓተ ኦሪት አባቶች ይጠቀሙባቸው የነበሩ ንዋየተ ቅዱሳት፡፡
  - ✓ የመጀመሪያው የከሳቴ ብርሃን አባ ሰላማ ትርጉም የሆነው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ፡
  - ✓ የቅዱስ ያሬድ ከህር የተሰራ ካባውና የመጀመሪያው በእጁ የጻፈው የድጓ መጽሐፍ፡
  - ✓ ግማደ መስቀል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡
- ነገር ግን በዚህ ጽሑፍ ያልተጠቀሱ ቅዱሳን ቦታዎች እና ቅርሶች በአሁን ሰዓት በአደገኛ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ በዘመኑ ያለን ክርስቲያኖች እነዚህን ምትክ የማይገኝላቸውን የሃገር ሃብቶች ተገቢውን እንክብካቤ ልናደርግ ይገባናል፡፡

መልመጃ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ ጻፉ፡፡

1/ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ስልጣኔ እንደነበራት እንዴት ማወቅ ይቻላል?

2/ ኢትዮጵያ ከህገ ልቦና ወደ ህገ ኦሪት እንዴት ተሸጋገረች?

3/ በኢትዮጵያ ከህገ ኦሪት ወደ ህገ ወንጌል እንዴት ተሸጋገረች?

4/ በአገራችን በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት እጅግ ብዙ አስደናቂ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የምታውቁትን ዘርዝሩ?

ምዕራፍ ሁለት

በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ የሚገኙ ታሪካዊ ገዳማት ማሳያ

2.1. አክሱም ጽዮን ማርያም

- ለኢትዮጵያ ክርስትና እናት ብቻ ሳትሆን ለስልጣኔ እና ለባህል መነሻ ምንጭ ናት ። የመጀመሪያው የአክሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን የተሰራዉ በቀዳማዊ ምንሊክ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ 1 ሺ ዓመት ገደማ ነው። አባቱን ንጉስ ሰሎሞንን ጎብኝቶ ሲመለስ በእግዚአብሔር ፍቃድ የቃል ኪዳኑን ታቦት የሙሴ ፅላት ለእኛ ለኢትዮጵውያን ተሰጥቶናል ። ከላይ እንደተገለፀው ቀዳማዊ ምንሊክ ታቦተ ጽዮንን ብቻ በማስመጣት አልተወሰነም ፤ ካህናተ ኦሪትን ከ 12 ሁለቱ ነገደ እስራኤል ሕዝብም ይዞ ነበር የመጣው።
- በአብርሃ ወአጽብሃ የአክሱም ቤተ መቅደስ ከመታነጹ በፊት ከከተማው ቦታ ላይ ታቦተ ጽዮን በህገ ኦሪት ተጠብቃ ትኖር ነበር።አሁን ፈርሶ የምናየው ቤተ-ክርስቲያን ፡ ከአያሌ ዘመናት በኋላ አብርሃ ወአፅብሐ በነገሱ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በ12 መቅደስ የተወሰነ አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን ተመሰረተ። ከላይ እንደተገለፀው ታቦተ ጽዮን በህገ ኦሪት ተጠብቃ ከኖረች በኋላ በአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬምናጦስ) አማካኝነት አዲስ በተሰራው ህንፃ ለመኖር ቻለች፡
- ጌታ የቆመበት አለት ላይ የእግሩ ጫማ ቅርፅ እስከ አሁን ሳይጠፋ በግልፅ ይታያል፡ ፡ ከዛ ወዲህ ቦታው መከየደ እግዚእ እየተባለ ይጠራል ።።።
- ይህ ውብ ቤተ-መቅደስ በዮዲት ጉዲት አማካይነት ተቃጥሎአል። ከዮዲት ጉዲት በመቀጠል የነገሰው አንበሳ ውድም በስደት ከሚኖርበት ሀገር ወደ ሃገሩ አክሱም ተመልሶ ኢትዮጵያን በሰላም ማስተዳደር ጀመረ። ይህ ንጉስ የክርስትና ሃይማኖት እንዲስፋፋ ያሬዳው ዜማ እንዲሁም ብሉይ እና ሐዲስ በትምህርት ቤት ተዘርግቶ እንዲነገሩ አወጀ። ይህን በጎ ስራ ካደረገ በኋላ የተቃጠለ ውብ ቤተ-ክርስቲያን ዳግም እንዲሰራ ካህናትም ሊቃውንቱን ሰብስቦ ሱባኤ ገባ። የለመኑትን የማይነሳ እግዚአብሔር ልክ ለአባቶቹ ለአብርሃ ወአፅብሃ እዳዘነበላቸው ሶስት ቀን ሦስት ለሊት ወርቅና እንቁ አዘነበላቸው በዚህም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ የህንፃ ባለሙያዎችን ሰብስቦ ሥራውን አስጀመረ ። በወርቅ በእንቁ አስጊጦ ቤተ-መቅደሱን አንጸ ጨርሶ

በአክሱም ሊቀ ካህናት አስባርኮ ቅዳሴ ቤቱን አከበረ፡፡ ነገር ግን ይህ ድንቅ መቅደስ በግራኝ አህመድ አማካኝነት በ 15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተቃጠለ፡፡

- ከዚህ በኋላ በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግስት ፈርሶ የነበረው ቤተ-መቅደስ አሁን በዘመናችን የምናየውን ቤተ-መቅደስ ለመስራት ችለዋል ፡፡ በመጨረሻም ታቦተ ጽዮን ወዳለችበት ቤተ-መቅደስ ሴቶች ስለማይገቡ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ አማካኝነት ቤተ-መቅደሱን እንደ አዲስ አሰርተው አስመርቀውታል፡፡

<u>መልመጃ</u>

1. አክሱም ርዕሰ አድባራት ወገዳማት የምትባለው ለምንድነው?
2. በአብርሃ ወ አጽብሃ ታንጻ የነበረው ቤተመቅደስ እንዴት ያለ ነበር?
3. ዮዲት ጉዲትን እና ግራኝ አህመድን ከአክሱም ጽዮን ቤተ መቅደስ ጋር ምን ያገናኛቸዋል ?
4. ሴቶች የማይገቡበት ቤተ መቅደስ የተሰራው በማን ነው?
5. አንበሳ ውድም እትጌ መነን ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ከአክሱም ጽዮን ጋር ምን ያገናኛቸዋል?

2.2. <u>ደብረ ዳሞ</u>

- ይህ ገዳም በትግራይ ክፍለ ሀገር በአድዋ አውራጃ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ገዳም ከሌሎቹ ገዳም ለየት የሚያደርገው ወደ ገዳሙ የሚመጣ ሰው በሙሉ ወገቡን በገመድ እየታሰረ የሚወጣበት መሆኑ ነው፡፡
- ይህን ስመጥር ገዳም የመሰረቱት ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከልን አንዱ የሆኑት አቡነ አረጋዊ /ዘሚካኤል/ናቸው ፡፡ ጻዲቁ የደብረ ዳሞን ተራራ ለብህትውና ከመረጡ በኋላ ወደ ተራራው ጫፍ ለመውጣት ተቸግረው ሳለ በተራራው ሥር ሆነው ወይኔ ምነው እንደ አሞራ ክንፉ በኖረኝ አለዚያም ምነው ገመድ በኖረኝ እያሉ ሱባኤ ገብተው ሲፀልዩ ሳለ ቅዱስ ሚካኤል ወደ እርሳቸው ቀርቦ “አትፍራ ሥልጣን ተሰጥቶሃል በበዓት ትንሽ አርፈህ ቆይ እግዚአብሔር በገመድ ፈንታ ትልቅ ዘንዶ ይልክልሃል አላቸው፡፡ ወዲያውኑ እግዚአብሔር በቅዱስ ሚካኤል አማካኝነት ቁመቱ ስድሳ ክንድ የሆነ ዘንዶ ልኮ በዘንዶውን ጭራ አቡነ አረጋዊ ተቀምጠው ዘንዶውም እንዳይተናኮላቸው ቅዱስ ሚካኤል ሰይፉን እየጠበቀ ትንሽ ወደ ተራራው ጫፉ እንደወረወራቸውና በተራራው ላይ ሲደርሱ

ሃሌ ሉያ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ በዚያ መቀመጣቸውን ገድለ አቡነ አረጋዊ ይገልፃል፡፡

- በአሁኑ ጊዜም የዚህ ዘንዶ ምሳሌ የሆነው የጠፈር ገመድ ይገኛል፡፡ ገመዱ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ እስከ አሁን ድረስም እንዳልተቀየረ የገዳሙ መነኮሳት ይናገራሉ፡፡ ሰፊ አገልግሎትም በመስጠት ይገኛል፡፡ ወደ ገዳሙ ለመውጣት መጀመሪያ ከላይ ወገቡን በሸምቀቆ ያስሩና ከዚያም ወፈር ያለውን እና በዘንዶው የተጠመለለውን የጠፈር ገመድ በእጅዎ ይይዛሉ፡፡
- ወደ ገዳሙ እንደወጡ የሚፈቀድላቸው ለወንዶች ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ሴቶች ወደ እዚህ ገዳም ለመውጣት ካለመቻላቸውም በላይ በገዳሙ የሚኖሩት ገዳማውያን ወንዶች በመሆናቸው ምክንያት ጸር እንዳይነሳባቸው ጭምር ነው፡፡
- በአፄ ገ/መስቀል አማካኝነት ወደ ገዳሙ መውጫ እንዲሆን ደረጃ ተሠርቶ ነበር፤ በኋላ ግን ደረጃው በአቡነ አረጋዊ አማካኝነት ፈርሷል ፡፡ ዳሞ የሚለውም የተራራው ስም የወጣው ከዚሁ ከደረጃው መፍረስ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ አባታችን አቡነ አረጋዊ በግእዝ ጻሕምሞ ማለትም አፍርሰው በማለት ስለተናገሩ ነው፡፡ ከጊዜ ብዛት ግን ዳሞ የሚለውን ቃል ፈጠረ፡፡ በዚህ ምክንያት የተራራው ስም ደብረ ዳሞ በመባል እየተጠራ ይገኛል፡፡
- ተራራውን ወጥተው እንደጨረሱ በወገቦ የታሰረውን ገመድ አውልቀው በአንዲት ጠባብ መሿለኪያ ውስጥ ያልፉና በተራራው ጥግ የተሠሩ ደረጃዎችን በጥንቃቄ ይወጡና በስተመጨረሻም ሣር እና ለምለም ሜዳን ያገኛሉ፡፡ በዚህ ሜዳ ላይ አንድ ቤተ-ክርስቲያን የተለያዩ የውሃ ጉድጓዶች በ3 የተከፈሉ የገዳማውያኑ መንደሮች እና የመቃብር ሥፍራዎች ይገኛሉ፡
- ቤተ-ክርስቲያኑ የታነጸው ጻዲቁ ከመሰወራቸው በፊት ስለነበር ቤተ-ክርስቲያኒቱ የተሰየመችው በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ነበር፡፡ የቤተ-ክርስቲያኒቱ የውስጠኛ ክፍል እጅግ በአስደናቂ ስዕሎች እና ውብ በሆኑ የእንጨት ሥራ ውጤቶች የተዋበ በዚህ የእንጨት ሥራ ተሰጥኦ እንደላቸው የሚነገርላቸው አፄ ገ/መስቀል ራሳቸው ሰርተውት እንደበሩ ይነገራል፡
- ሌላው በቤተ-ክርስቲያኒቱ ቅፅር ግቢ የሚገኘው የፀበል ቦታ ነው፡፡ አራት መዓዘን ባለው የድንጋይ ገንዳ የሚገኝ ሲሆን ከብዙ በሽታዎች የመፈወስ ኃይልም አለው፡፡

- በሌላ በኩል በገዳሙ ውስጥ የሚገኝ አንድ መነኩሴ በቤቱ ውስጥ አንድ የፀሎት ቤት፣ አንድ እንግዳ መቀበያ ሳሎን፣ አንድ ማዕድ ቤት ከነምንጭ ውኃው ይኖረዋል ነገር ግን ይህ የምንጭ ውኃ የሌላቸው ቤቶች ከጎረቤት በቀጭን ቦይ ውኃ ስለሚያገኙ የውኃ ችግር አያጋጥማቸውም፡

መልመጃ

1. ወደ ደብረ ዳሞ የሚውጣው እንዴት ነው? ለምን?
2. ደብረ ዳሞ ገዳምን የገዳሙት አባት ማናቸው? ከየት ነው የመጡት? ለምን ?
3. አጼ ገብረ መስቀል እና ደብረ ዳሞ ገዳም ምን ታሪካዊ ሂደት ያገናኛቸዋል ?
4. የደብረ ዳሞ ተራራን ወጥታችሁ ስትጭርሱ ምን ታገኛላችሁ በዝርዝር ግለጹ?

2.3. ደብረ ማርያም

- ደብረ ማርያም ቆርቆር ከሐውዜን ከተማ በስተደቡብ -የምትገኝ ጥንታዊት ቤተ-ክርስቲያን ናት፡፡ ከተራራው እግር እስከ ቤተ-ክርስቲያኑ ድረስ የአንድ ሰዓት የእግር ጉዞ ይጠይቃል፡፡ ተራራ መውጣት ተፈጥሮን ማድነቅ ለሚያስደስታቸው ሰዎች ደብረ ማርያም ቆርቆር ተስማሚ ናት፡
- ትላልቅ ከሚባሉ የትግራይ ውቅር ቤተ-ክርስቲያን መካከል የምትመደብ ስትሆን የቤተ-ክርስቲያኑ ፊት ለፊት በጭቃና በድንጋይ የተሠራ ግንብ ተሰርቶለት ይታያል፡፡
- የውጫዊ አካሉ ጣራ በእንጨት የተሠራ ሲሆን አራት መስኮቶች ወደ ውስጥ የሚያዘልቅ ሁለት በሮች አሉት፡፡ እንዲሁም ስድስት አምዶች አሉት፡፡ ቤተ-ክርስቲያኑ ውስጥ በሚያስደነቅ ጥበብ የተቀዱ የንስር መልክ ያላቸው ንድፎች በግድግዳው ላይ ይታያሉ ጣራውም በተለያዩ ንድፎች የተንቆጠቆጠ ነው፡፡ እንዲሁም የሐዲስ ኪዳን ታሪክ የሚያንፀባርቁ ስዕሎች አሉበት፡፡ ለምሳሌ ያህል ወደ ኢየሩሳሌም የተደረገን ጉዞ የሚያንፀባርቁ ሥዕሎች ይገኛሉ፡፡

መልመጃ

1. ደብረ ማርያም/ቆርቆር ማርያም የት ትገኛለች?
2. የደብሩ ስያሜ ስለቤተክርስቲያኑ አሰራር የሚነግረን ነገር ምንድን ነው?
3. ከተራራው ስር እስክ ቤተክርስቲያኑ በእግር ጉዞ ስንት ሰዓት ይወስዳል?

4. በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙ ሥዕላትን ዘርዝሩ?

2.4. አቡነ ይምዓታ

- ጻድቁ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመካከለኛው ምስራቅ በስደት ምክንያት ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ወንጌልን ያስተምሩ ከነበሩት ዘጠኙ መነኮሳት መካከል አንዱ ናቸው፡ ፡በትግራይ ገርዓልታ አካባቢ በሚገኘው ልዮ ስሙ ጎሕ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በስማቸው የታነፀው ቤተ-ክርስቲያን ይገኛል፡፡መገኛውም ከሐውዜን በስተ ደቡብ 13ኪ.ሜ ከተጓዙ በኋላ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ የግማሽ ሰዓት የእግር ጉዞ ማድረግ ይጠይቃል፡፡
- ቤተ-ክርስቲያኑ ከፍታ ቦታ ላይ ስለሚገኝ የአለት ተራራው ላይ ለመውጣት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን ለእግር እና ለእጅ መቆንጠጫ የሚያገለግሉ ጉድጓዶች አሉት ወደ ተራራው ከተወጣ በኋላ በጣም በሚያስፈራ ገደል የተከበበችና ሃይለኛ የአየር ግፊት ያላት አንዲት ጠባብ መንገድ ትገኛለች፡፡
- ቤተ-ክርስቲያኑ ከአለት ተፈልፍሎ የተሠራ ሲሆን ከውስጥ አራት ራሳቸው ችለው የቆሙ ዓምዶች አሉት፡፡ እንዲሁም በውስጡ ጥንታዊ እና እጅግ ደማቅ የሆነ ሥዕሎችን ይዟል ይህ ቤተ-ክርስቲያን በተራራዎች ጉያ የተሸጎጠ በመሆኑ ከግራኝ እና ከጉዲት ጦር ሊያመልጥ ችሏል፡፡ የአቡነ ይምራት ገዳም የመዘረፍም ሆነ የመቃጠል እድል አላጋጠመውም፡፡ የአቡነ ይመዕታ ቤተ-ክርስቲያን ሀገራችን ካሉት የውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ ነው፡

መልመጃ

1. የአቡነ ይምዓታ ገዳም የት ነው የሚገኘው?
2. አቡነ ይመዓታ ወደ ኢትዮጵያ በምን ምክንያት መጡ? በስንተኛው ክፍለ ዘመን?
3. የአቡነ ይምዓታ ገዳም አሰራር አብራሩ ?
4. የአቡነ ይምዓታ ገዳም በዮዲት ጉዲት እና በግራኝ አህመድ ምንም ዓይነት ጉዳት ያልደረሰበትን ምክንያት አስረዱ

2.5. አባ ጳንጠሌዎን

- በትግራይ ክፍለ ሃገር የሚገኝ ታላቅ ገዳም ነው፡፡ አክሱም አጠገብ በሚገኝ ተራራ ላይ በሚያስደንቅ እይታ የሚገኝ ቤተ-ክርስቲያን ነው፡፡አባ ጴንጠሌዎን ከዘጠና ቅዱሳን መካከል አንዱ ሲሆኑ የመሰረቱትም እሳቸው ናቸው ነገር ግን እኚህ ቅዱስ በአካለ ሥጋ በነበሩት ወቅት በማርያም መግደላዊት የሚጠራ ቤተ-ክርስቲያን ነበር፡፡

- ከአባ ጴንጠሌዎን በኋላ ግን መካነ ሰማዕት በመባል ይታወቃል፡፡ እንዲሁም በጻድቁ ስም በተደራቢነት ይጠሩበታል፡፡
- መካን ሰማዕት ለወንዶች አገልግሎት ሲሰጥ በማርያም መግደላዊት የተሰራው ቤተ-ክርስቲያን ግን ለሴቶች ብቻ ተወሰኖ እስከ አሁን ድረስ ይገኛል፡፡
- የቦታው ስያሜም አባ ጴንጠሌዎን ዘሰማዕት ይባላል፡፡ አንዳንዴም መካነ ሰማዕት በመባል ይጠራል፡፡ በአካባቢው የሚኖሩ ምዕመናን እንዳ አባ ጴንጠሌዎን እያለ ይጠሩታል፡፡
- አፄ ካሌብ ወደ የመን ከመዝመታቸው በፊት ከአባ ጴንጠሌዎን የፀሎት ተማፅኖን ያገኙበታል በድል አድራጊነት ሲመለሱ መንኩሰው የተቀመጠበት በኋላም አፅማቸው ያረፉበት ገዳም ነው፡፡ ገዳሙ በከፍታ ቦታ ላይ ሲለሚገኝ ለአምስት ዓመት የጣሊያን ምሽግ ሆኖ ነበር፡፡

<u>መልመጃ</u>

1. የ፱ቱ ቅዱሳን ገዳማት በርካቶቹ በአክሱም አካባቢ መገኘታቸው በዘመኑ ስለነበረው ሁኔታ ምን ያስተምረናል፡፡
2. የአባ ጳንጠሌዎን ገዳም መጠሪያዎ ስንት ናችው ዝርሯቸው ?
3. አጼ ካሌብ ወደ የመን ከመዝመታቸው በፊት እና ከድል በኋላ በአባ ጴንጠሌዎን ገዳም ምን ምን ተግባራትን ፈጸሙ? ለምን?
4. የአባ ጴንጠሌዎን ገዳም ታሪካዊ ዋጋ ከፍ ከሚያድርጉት ነጥቦች ሦስቱን ግለጹ?

2.6. <u>ማኅበረ ዶጌ</u>

- ይህ ገዳም የሚገኘው በትግራይ ክፍለ ሃገር ሲሆን በአክሱም አውራጃ በስተደቡብ በሚወሰደው መንገድ ላይ ይገኛል፡፡ የተገደመው በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግስት ሲሆን የገደሙትም ራሳቸው መሆኑ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡
- በዚህ ገዳም እጅግ አስደናቂ የሆኑ ታሪኮች የታዩበት ነው፡፡ በስፍራውም በእጅ የሚዳሰሱ ተአምራት የታየባቸውና የተደረገባቸው ሁሉ በቅርሰነት ተጠብቀው ይገኛሉ፡፡

  ለምሳሌ፡-

  - ጌታችን የተቀመጠበትና የቆመበት ድንጋይ ከነ ምልክቱ
  - “ ምስዋሮም ” የሚባል ጻድቃኑ የተሰወሩበት ሥፍራ

- ጌታ ከድንጋይ ላይ ሆኖ ዘንግ ወርውሮ ያፈለቀው ውኃ
- ጻድቃኑ ሲወቅጡበት የነበረው የድንጋይ ሙቀጫ፡፡
- ከሮም የመጡ ባለ መስታወት ቀዋሚ መስቀል፡፡
- ርዕሰ ዮሐንስ የሚባሉ ነገሥታት ከነዘዉዳቸው ጻጻሳት ከነአክሊላቸው የተሳሉ ስዕል፡፡
- ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ ማህበር ዓድቃን (ዶጌ) ውስጥ ሆኖ ያስተማረበት እና ያጠመቀበትን ሁኔታ የሚያሳይ ስዕል፡፡
- ሌሎች አስደናቂ ቅርሶች የሚገኙበት ታላቅ ገዳም ነው፡፡

<u>መልመጃ</u>

1.ማህበረ ዶጌን የገደሙት ማን ናቸው ?

2.በገዳሙ ከሚገኙት ቅርሶች ከጌታችን ጋር የተገናኘ ተአምራት የተሰራባቸው ስንት ናቸው ?

3.በማህበረ ዶጌ ምን ዓይነት ሥዕላት ይገኛሉ?

4.በማህበረ ዶጌ ከሚገኙ ቅርሶች የትኛው አስደነቂ ነው? ለምን?

ምዕራፍ ሦስት

በጎንደር የሚገኙ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያት ማሳያ

- እንደሚታወቀው ጎንደር ታላላቅ የኢትዮጵያ ነገሥታት ነግሰውበታል ፡፡የሊቃውንት ምንጭ ናት፡፡ይህች ከተማ የመላ ኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነበረች፡፡ የነገሥታቱ መኖሪያ የመሳፍንቱ መሰብሰብ ለመላ ሀገሪቱ የሚደርስ አዋጅ የሚታወጅባት ትልቅ ከተማ ነበረች ፡፡
- ዋና ከተማ የሆነቸው ግራኝ መሐመድ ከተሸነፈ በኋላ በአፄ ሠርፀ ድንግል /1563-1597/ ዘመን መንግሥት ነው፡፡ቆይቶም አፄ ፋሲል ሲነግሥ /1632-1667/ ጎንደር ማዕከላዊ መንግሥትነቷ ጸንቷል ፡፡ከዚህም የፋሲል ቤተ መንግሥት /ፋሲል ግንብ/ የአድያም ሰገድ ኢያሱ ቤተ መንግስት ተሠርቶባታል፡፡44ቱ ታቦታትም በከተማዋ ተተክለውባታል፡፡

3.1. ጎንደር ቅድስት ሥላሴ

- ስለ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ስናነሳ አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድን ማውሳታችን የግድ ይሆናል ፡፡የደብር ብርሃን ሥላሴን ታሪክ ከ አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ነጥሎ ማየቱ ታሪኩን ያደበዝዘዋል፡፡አፄ ፋሲል ጻድቁ ዮሐንስ ደግሞ ዛሬ ታሪኩን በመጠኑ የምናያው አድያም ሰገድ ኢያሱ ይወልዳል ፡፡እንግዲህ አፄ ኢያሱ የደጋጎቹ ነገሥታት ልጅ መሆኑ ነው፡፡
- አፄ ዮሐንስ ልጃቸውን ኢያሱን በትሕርምትና በሥርዓት በገዳም እንዲድግ በመፈለጋቸው አፄ ሠርፀ ድንግል ባቀኑት በአርማጭሆ ወደሚገኘው ታልቅ ገዳም ደብረ ሞረና ላኩት፡፡በዚያም በገዳሙ ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ሥርዓተ ቅዳሴ ፤ዜማ ዳዊት አጠናቅቀው ካወቁ በኃላ የገዳሙ አባቶች ይህንን ልጅ አስተምረነዋል ብለው ወደ አባታቸው ሰደዷቸው፡፡
- አፄ ዮሐንስም ‹‹ሌላስ ምን ተምሯል?››ብለው ይጠቃለ፡፡ሌለማ ምን እናስተምረው?ይሏቸዋል የገዳሙ አለቆች ‹‹እንጀራ መጋገር፣ የአባቶች እግርና ልብስ ማጠብ ፣ሌላም በገዳሙ ያለ ተግባራት አስተምራችሁታል?›› ብለው በድጋሚ ቢጠይቁ ‹‹ይሄንንማ የጌታችንን ልጅ እንዴት እናዝሃለን ሌላ አርድእት መቼ ታጣና››ይሏቸዋል ጻድቁ ንጉሥም ‹‹እንግዲያማ ትዕቢት ነው አስተምራችሁ

ያመጣችሁልኝ ብሉ መልሳችሁ ውሰዱት እናንተ መነኮሳት የምትሠሩትን ሥራ በገዳሙ ያለውን ሥርዓት ሁሉ አስተምራችሁ ላኩልኝ››ብለው መልሰው ሰደዷቸው፡

- ከዚያም ኢያሱ በገዳም ያለውን ሥርዓት አጠናቅቆ ተምሮ መጣ፡፡አባቱም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ኃላፊነት ይሰጡታል፡1674ዓ.ም ኢያሱ የንግሥና መንበሩን ከአባቱ ይረከባል፡፡አሁን ኢያሱ ንጉስ ሆኗል፡፡ አፄ ኢያሱ በነገሠ በአሥራ ሁለተኛ ዐመቱ በ1686 ዓ.ም በጎንደር ከተማ የሚገኛውን የደብረብርሃን ሥላሴ ቤተክርስቲያን አስተከለ፡፡በዚሁ ዓመት መቃረብያ ተሠርቶ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ፡፡
- ታቦተ ሕጉም በመቃረቢያ ውስጥ ለሁለት ዓመት ቆይቶ የዋናው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ጀመረ በ1688 ዓ.ም የሕንፃው ሥራ ሲጠናቀቅ ወደ አዲሱ ሕንፃ ገብቷል፡፡ቤተክርስቲያኑ የተሠራበት እንጨት በጣም ትላልቅ ነበረ፡፡በዚያን ጊዜ በምን መጓጓዣ ሞኑው እንዳመጡት ላስተዋለ ያስገርማል እንጨቱ የመጣው ገሚሱ ከዘጌ ነው ሲል የተቀረው ደግሞ ከአርማአኞሆ እንደሆነ ይነገራል፡፡የቀድሞ ሕንፃው ክብ ሲሆን ሦስት መቅደስ ነበረው፡፡የበሩ/ሳንቃዎች/ ሲከፍቱ አይታዩም ተሸከርክረው ወደ ውስጥ ወደ ግድግዳው ነበረ የሚገቡተ፡፡አፄ ኢያሱ ቤተ ክርስቲያኑን ካሠሩ በኃላ ታቦተ ጽዮንን ወደ ጎንደር ለማምጣት ወደ አክሱም ጎዞ አድርገው ነበረ፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ለማምጣት ሳይቻላቸው ቀርቷል፡
- ከዚህም አብረዋቸው የተጋዙት አባ ስብሐት ለአብ የሚባል ሰው ሕዝቡ በርሃብ ሊያልቅ ሲል ታቦተ ጸዮንን ማምጣት ባይሳክልን ለምን ታቦተ ሥላሴን አናስገባም አሏቸው፡፡በዚሁ ተስማምተው ታቦተ ሥላሴ እንዲገባ አድርገዋል፡፡የአክሱም ታቦተ ጽዮንም ለድብረ ብርሃን ሥላሴ ግብር እንድታስገባው ግብር ጥለውበት ተመልሰዋል፡ ፡አፄ ኢያሱ ወደ ሸዋ ደብረ ብርሃን ተጉዘው ሊቃውንቱንና ባለባቱን ጠይቀው ደብረ ብርሃን የሚለውን ስም ለመሰየም ፈቃድ ሲያገኙ ብዙ ወቄት ወርቅ ሰጥተው ተመለሱ፡፡ይህንን ስያሜ የመረጡበት ምክንያትም ቦታው ብርሃን የወረደበት በመሆኑ በሁኔታው ተማርከው እንደሆነ ይነገራል፡፡
- በዚህ ደብር መጀመሪያ የተሾመው ቀውስጦስ ነበሩ፡፡የደብርም የመጀመርያ የማዕረግ ስም ሊቀ ካህናት ነበረ፡፡ወዲያውም ተለውጦ መልአከ ብርሃን ሆኗል፡፡ቀውስጦስም ያረፈው በ1716 ዓ.ም በ85 ዓመቱ ዕድሜው ነበረ፡

- በሌላ ብኩል በመቅዳሱ ውስጥ የሚግኙት ቅዱሳን ስዕላት እጅግ የሚያስደምሙ በዛምኑ የነብሩ አበው ጥበብ ምን ያህል እረቂቅ እንደንበር የሚመሰክር ሕያው ምስክር ነው

መልመጃ

1. የደብረብርሃን ስላሴን ያስተክለት አፄ ኢያሱ ማናቸው?
2. የደብረ ብርሃን ስላሴ ስሙን እንዴት አገኘ አፄ ኢያሱ ለምን ወደ ሸዋ ደብረብርሃን መጡ?
3. የአፄ ኢያሱ አባት ጻድቁ ዩሐንስ ልጃቸወን ደግመው ወደገዳም የላኩበት ምክንያት ምንድን ነው?
4. ከአፄ ኢያሱ ታሪክ ምን ትምህርት አግኛችሁ

3.2. ዙር አምባ

- ዙር አባ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም በደቡብ ጐንደር ሀገረ ስብከት በላይ ጋይንት ወረዳ ዙር አባ ቀበሌ ገብሬ ማህበር ከባሕር ዳር ወደ ንፋስ መውጫ በሚወስደው መንገድ 150ኪ.ሜ ላይ ከምትገኘው ሣሊ/ሠዓሊ/ ከምትባለው መንደር በስተ ምስራቅ ገሊላ ተብሎ በሚጠራው ተራራ ላይ የሚገኘው ገዳም ነው።።ገዳሙ በስድሰተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአቡነ አረጋዊና በቅድስና ያሬድ አማካኝነት ተመስርቷል።። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የተሰራች በመቤታችን በቅድስት ድንግል ማሪያም ስም ነው።።
- ቅዱስ ያሬድ በቦታው ከርሞ አይድረቅ በምትባል ዛፍ ስር ተቀምጦ ዝማሬ መዋሥዕትን ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ስላስተማረባት የህቺ ገዳም የዝማሬ መዋሥዕት ማስመስከሪያ ቦታሆነች ።። አፄ ገ/መስቀልም ቤተ ክርስቲያኑ እስኪሰራ ለሦስት አመት የተቀመጡበት ቦታ ዛሬ አፄ ከተማ ይባላል።። አቡነ አረጋዊ 640 የሚሆኑ መነኩሳትን ሰብስበው አፈላ ዮሐንስ የሚባሉትን አባት ሰይመው ወደ አክሱም ሄደዋል።።
- በግራኝ አህመድ ወረራ ገዳሙ ሕዳር 20 ቀን 1521 ዓ.ም ተቃጥሏል።። 60 የሚሆኑ መነኮሳትና ዐርባ የሚሆኑ ካህናት የልዳታ ለማርያምን ጽላትና ሌሎች ንዋያተ ቅዱሳትን በመያዝ ከገቡበት ዋሻ ውስጥ ተሰውረው ቀርተዋል።።ዋሻው እስከ አሁን

ድረስ ያለ ሲሆን አንዳንዴ የቆሎ ተማሪዎች ቅኔ ለመቁጠር ሲሄዱ ነብርና ያልተለመዱ ድምጽ እንደሚሰሙ ይናገራሉ፡፡

- ቤተ ክርስቲያን ከተቃጠለ በኃላ ለሠላሳ ዓመታት ያህል ያለ ምንም አገልግሎት ተዘግቶ ቆይቷል ፡፡ንጉሡ ዐፄ ሠርፀ ድንግል ከቃጠሎው ከተረፈው መቅደስ ቀጥለው ቅድስቱንና ማህሌቱን አሠርተው የቀረውን አስጠግነዋል፡፡
- ገዳሙ ከተመሠረተ ጀምሮ 69 አባቶች በመምህርነት /በአበምኔትነት/ ተሾመዋል ፡፡ በገዳሙ በግራኝ ጊዜ ከቃጠሎ የተረፉ ብዙየብራና መፃሕፍትና ከዚያ ጊዜ ወዲህ መኳንንትና ነገሥታት ለገዳሙ ያበረከቷቸው የብርና የወርቅ ካባዎች አክሊሎች፣ ደወሎች እንዲሁም የቅዱስ ያሬድ የብር መቋሚያ፣ ጽናጽልና ንዋያተ ቅድሳት ይገኛሉ፡፡
- በዚህ ገዳም ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለስድስት ዓመታት ያህል ተቀምጠዋል፡፡ ይህ ገዳም በኢትዮጲያ ብቸኛ የሆነው የዝማሬ መዋሥዕት ማስመስከርያ ትምህርት ቤት/ጉባኤ ቤት/ ነው፡፡

3.3. ዋሻ እንድርያስ ገዳም

- በሰሜን ጐንደር ሀገረ ስብከት የሚገኝ ገዳም ነው፡፡ገዳሙ የተገደመው በአስራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ ይኩኖአምላክ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ይህ ዋሻ ገዳም በገዳምነቱ ከመታወቁ በፊት በዘምነ ኦሪት የዘንዶ አምልኮ የፈጸምበት እንደ ነበር ይነገራል፡፡ይህንን ሥርዓተ አምልኮ በመሻር አቡነ እንድርያስ የክርስትናን ሃይማኖት በማስተማር በዋሻው የኢየሱስ ታቦት አስገብተው ገዳም መሠረቱ፡፡
- በሰሜን ጐንደር ሀገረ ስብከት የሚገኝ ገዳም ነው፡፡ገዳሙ የተገደመው በአስራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ ይኩኖአምላክ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ይህ ዋሻ ገዳም በገዳምነቱ ከመታወቁ በፊት በዘምነ ኦሪት የዘንዶ አምልኮ የፈጸምበት እንደ ነበር ይነገራል፡፡ይህንን ሥርዓተ አምልኮ በመሻር አቡነ እንድርያስ የክርስትናን ሃይማኖት በማስተማር በዋሻው የኢየሱስ ታቦት አስገብተው ገዳም መሠረቱ፡፡
- ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዋሻው በስማቸው ዋሻ እንድርያስ ተባለ በገዳሙ ውስጥ ለዘንዶው ወተት ይቀርብበት የነበረው ከእንጨት የተፈለፈለ ገንዳ የሰው ቅርጽ ያለው የእንጨት ምስልና አያሌ ጥንታውያን መጻህፍት ይገኛሉ፡፡

- አቡነ እንድርያስ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዝሙር የነበሩ የዋሻ እንድርያስ ገዳም መሥራች ናቸው፡፡የትውለወድ ሀገራቸው ሸዋ ሲሆን በትምህርት እየተኮተኮቱ ያደጉት በደብረ ሊባኖስ ገዳም ነው፡፡አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሄዱበት ሁሉ ያስከትሏቸው ነበር፡፡አቡነ ተክለሃይማኖት ወደ ጐንደር በመጡ ጊዜ አቡነ እንድርያስን አስከትለዋቸው ነበር መጥተው ነበር ፡፡
- ጻድቁ ወደ ደብረ ሊባኖስ ከተመለሱ ከጥቂት ጊዜ በኃላ አቡነ እንድርያስን ወደ አካባቢው እርሳቸው የጀመሩትን እንዲያጠናክሩ ላኳቸው፡፡አቡነ እንድርያስ በጎንደር እያታዋወሩ ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻም ወደዚህ ዋሻ በመምጣት በቦታወ ይፈጸም የነበርውን የዘንዶ አምልኮ አጥፍተው ቤተ መቅደስ አደርጉት፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ በሚገባው አደራጅተው ሕዝቡንም አስተምረው ሲፈፅሙ እብናት ወዳለው ደብረ ተክለ ሃይማኖት ገዳም በመምጣት በተጋድሎ ቆይተው እዚሁ አርፈዋል፡፡

3.4. ዋሻ ተክለሃይማኖት

- ይህ ቤተ ክርስቲያን ከአዲስ ዘመን ወደ ጐንደር በሚወስደው መንገድ አቅራቢያን የሚገኝ ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ የአካባቢው መጠሪያ ስምም ጣራ ገዳም እየተባለ የሚጠራው ነው ይህንን ገዳም የአካባቢው ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ልዩ ውብት ስጥቶታል፡፡ነበተለይ ገዳሟ ያለችው ዙሪያው ገደላማ ሆኖ ጥቅጥቅ ባለ ደን በተሸፈነ ቋጥኝ ስር ነው፡፡ ገና ወደ ዋሻው ውስጥ ሳይገባ በጭቃና በድንጋይ ውብ ሆኖ የተሠራውን የተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ያገኙታል፡፡
- የዚህን ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት እንደ ተረዳነው ከሆነ የገዳሙ ሥራ በአፄ የኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ተጀምሮ በአፄ ሰይፈ አርዕድ ነው የተጠናቀቀው፡፡ ዋሻው የውስጥ ለውስጥ መንገድ አለው፡፡ በዚህ የውስጥ ለውስጥ መንገድ አቡነ እንድሪያስ እና አቡነ ተክለሃይማኖት ከበዓታቸው ተነስተው ዛና ማርያም ድረስ በመሄድ ጸሎት ያደርጉ እንደነበር የቤተ ክርስቲያኗ አበው ይናገራሉ፡፡ በዋሻው ውስጥ ከመንገዱ ሌላ ባህርም አለ ነው የሚባለው፡
- በዋሻው ውስጥ ከመንገዱ ሌላ ባህርም እንዳለ ነው የሚነገረው፡፡ ከባህሩም በኋላም ጥንታዊ የሆኑ ከወርቅና ከብር የተሰሩ ቅርሶችና መጽሐፎች እንደሚገኙም ነው የነገራል ፡፡

- በወረራው በኢጣሊያ መንግሥት የዚህን ቤተ ክርስቲያን ቅርስ ያለምንም ከልካይ ግፍ በተሞላበት ሞኳኔ ያለ ርህራሔ ብዙ ቅርሶችን እንደ ተዘረፉ የቤተ ክርስቲያኒቱ አበው በቁጭት የሚናገሩት ነው።

ምዕራፍ አራት

በወሎ የሚገኙ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያት ማሳያ

- ወሎ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል እንደፊርጥ ሆና ከአክሱም ዘመን በታላ እስክ በመካከለኛው ዘመን የአገራችን እና የቤተክርስትያናችን ታሪክ እንበርት የስልጣኔና የመንፍሳዊንት ልዕልና ከፍታ የነበረበት ። አለምን ያስደንቁ ብርካታ ደነቅ ቅርሶች የሚገኙብት ። ከፍለ አግር ነቸ ።

4.1. የቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያንናት ታሪክ

- ቅዱስ ላሊቢላ ከአባቱ ከንጉስ ኂን ስዩም እና ከእናቱ ከንግሥት ኬርወርና መኃቢት 28 ቀን 1109 ዓ/ም ተፀነሰ ታህሳስ 29 ቀን 1110 ዓ/ም ተወለደ። ቅዱስ ላሊበላ ሦስት ስሞች እንደ ወጡለት ሊቃውንት ያስረዳሉ እነዚህም። ላሊበላ፡ዘርዓ ስምዖን እና ገብረ መስቀል ናቸው።
- ላሊበላ የሚለውን ከመፀነሱ በፊት የእግዚአብሔር መልአክ ለወላጆቹ በራዕይ ተገልፆ ወንድ ልጅ እንደሚወልዱና ስሙም ላሊበላ ተብሎ እንደሚጠራ እንዳበሰራቸው ገድለ ላሊበላ ያስረዳል።
- ቅዱስ ላሊበላ በተወለደ ጊዜ የንብ ሰራዊት ወደ ቤተ መንግሥቱ መጥቶ የህፃኑን መላ አካላትና ዙርያውን ከበበውእናቱ ይህንን አስደናቂ ነገር ተመልክታ ልጇን ንብ ከበበው ልጄ ማር ይባላል እያለች የእግዚአብሔር መልአክ የተናገሩትን በማስታወስ ላሊበለ ብላዋለች።።ላል ማለት በአገውኛ ቋንቋ ንብ ማለት ናት።
- ዘርዓ ስምዖን ፡ የክርስትና ሰሙ ሲሆን ላሊበላን ስመ መንግሥቱን ገብረ መስቀል ብሎ እንደሰየመው ገድሉ ያስረዳል።
- ላሊበላም በስይጣን ተንኰል አነሳሽነት ከቤተሰቦች ባጋጠመው ፈተና ምክንያት ከበው ጋር ከመኖር ከሰራዊት ጋር መኖር ይሻላል ብሎ ወደ ሌላ ቦታ ተሰደደ ከዚያም

አካባቢውን በመልቀቅ በልደት ላይ እንዳለ በመልአኩ መሪነት በግብፅ እና በኢየሩሣሌም የሚገኙትን ቅዱሳን መከናት ቦታዎችን ለመሣለም ተሣልሞ እግዚአብሔርም ተገልያለት ብዙ የምህረት ቃል ኪዳን ከተናገረው በኃላ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

- የመንግሥትነት ሥልጣን ከወንድሙ ከንጉስ ሀርቤ ገብረማርያም ተቀብሎ በኢየሩሳሌም የሚገኙት ቅዱሳን መካናት በአንድ አካባቢ አዲገኙ ለማድረግ በተወለደ በ57 አመቱ በነገሠ በአስረኛው አመቱ 11 ቤተ መቅደሳችን ከ ቋጥኝ ድንጋይ ላይ ፈልፍሎ እና ቦርቡሮ እንደሚያንፅ ዝርዝር ቤተመቅደሶቹን ገና ሣይታነፁ በስዕል መልክ ስለ አሣየው በደስታ እየዘለለ ምስጋና ለአምላኩ በማቅረብ ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ ወደ ላስታ ሮሐ ጉዞውን ቀጥሎ ምድረ ሣይ ከምትባለው ቦታ ላይ ውሃ ፈልቆሎት በዚያ አደረ፡፡
- በዚች ሌሊትም እግዚአብሔር ለንጉሥ ሀርቤን በህልሙ ተገልያ በወንድሙ በቅዱስ ላሊበላ ላይ የፈፀመውን በደል እያስታወሰው ከወቀሰው በኃላ የንግሥናውን ሥልጣን ለላሊበላ እንዲያስረክበውና ስመ መንግስቱም ገብረ መስቀል ብሎ እንዲሰይመው በመንገድ ላይም እንዳለ ሄዶ እንዲቀበለው እና ሥርዓትም ሰርቶ እለቱን እንዲያነግሰው ስለ ነገረው ሰራዊቱን አስከትሎ በእግሩ ተግዞ ቅዱስ ላሊበላ ካደረበት ቦታ በመድረስ ይቅርታ ጠይቆ በክብር ተቀብሎ እለቱንም አንግሶታል፡፡
- ከዚህም በኃላ ላሊበላ መካነ ልዕልት ከምትባል ቦታ አጠገብ ቀይት ከምትባል ሴት በገንዘቡ መሬቱን ገዝቶ የቦታውን አቀማመጥ በመመልከት በተፈጥሮ ቋጥኝ ድንጋያማ የሆነ ቦታ ላይ ከላይ ወደ ታች እየጠረበ እና እየቦረበረ በሀረግና በመስቀል ጌጥ በማስጌጥ 11(አስራ አንድ) ቤተ መቅደሶችን አንፆአል (ሰርቷል)፡፡
- በጥቅሉ ላሊበላ በኢትዮጲያ ውስጥ ያነፃቸው ከ40 ያላነሱ ናቸው፡፡ሲሉ አንዳንድ ፀሐፊዎች ደግሞ 23 ፍልፍል ህንፃዎች ናቸው ይላሉ፡፡
- ቅዱስ ላሊበላ ያነፃቸው ቤተ መቅደሶች ዝርዝርና አሰራር ባጭሩ እንመለከታለን

1. <u>ቤተ ማርያም</u>

- ቅዱስ ላሊበላ የስራው መጀመርያ ያደረጋት ይችን ቤተ መቅደስ ነው፡፡የቤተማርያም የውጪ ቁመት 13 ሜትርከ 39 ሳ.ሜ ሲሆን በሚያስደንቅ ሀረግ አስጊጦ ሰርቶታል፡ ፡ቤተ ማርያም የሰባተኛው ሰማይ የጽርሐ አርያም ምሳሌ ናትለመንበተ ስብሀት እንደ

ጠፊር ናት፡፡ልዑል ማደያርው ቀደሰ እግዚአብሔር በመካከል ነውና፡፡አትናወጽም እንዳለ መዝ 45፤5

- በዚህች ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚየስደንቅ ከመሬት እስከ ጣሪያ የሚደርስ አምደ ብርሐን አለ፡፡በየአመቱ ታህሳስ 29 ቀን የሚከበረው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እና የቅዱስ ላሊበላ የልደት በዓልም ሥርዐቱም የሚከናወነው በዚሁ በቤተማርያም በቤተክርስቲያኑ ዙርያ ማሜ ጋራ በሚባለው ገደል አፋፉ ላይ ሆነው ሊቃውንቱ ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ዛሬ ተወለደ እለ ሻማ ካባና ጥንግ ደርብ ለብሰው ሲዘምሩ የሰማይ መላዕክት እንጂ ምድራዊያን ሰዎች አይመስሉም፡፡

2. <u>ቤተ መድኃኔዓለም</u>

- ይህ ቤተመቅደስ ከቤተማርያም በስተሰሜን ምስራቅ በኩል ጐንለጐን የሚገኙ ሲሆን ሦስት ቤተ መቅደሶች አሉት፡፡በስፋቱም የመጀመርያወን ይይዛል፡፡
- ቤተመድኃኔዓለም የሰማይ ውዱዱ ምሳሌ ነው ይባላል ቤተመድኃኔአለም 72 አዕማዶች አሉት 4 ምሰሶዎች አሉት፡፡በዚሁ ቤተመቅደስም ሌላውና አስደናቂው ነገር አፍሮ አይገባ የተባለው ክቡር መስቀል በውስጡ ይገኛል፡፡

3. <u>ቤተ ደብር ሲና</u>

- ይህ ቤተ መቅደስ ከቤተጐለጐታ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

4. <u>ቤተ ጐለጐታ</u>

- ይህ ቤተመቅደስ ቁመቱ 8 ሜትር ከፍታ ከ15ሳ.ሜ ሲኖረው ወርዱ 8 ሜትር ነው፡ ፡በግድግዳው ላይ የ12ሐዋርያት ስዕል የተቀረፀ ሲሆን የሻሸ፤የመስቀል እና የመፀሐፍ አያያዝ ሣይቀር ምልክት የሚያመለክት ቅርፅ ያለው ነው፡፡

5. <u>ቤተ መስቀል</u> ፡-

- ይህ ቤተ መቅደስ ከቤተ ማሪያም በሰተ ሰሜን የሚገኝ ሲሆን ታቦተ መስቀል ያለበት ቤተ መቅደስ ነው፡፡
- ቤተ መስቀል በውስጡ 4 ትላልቅ ዋሻ ያለው ነው፡፡

6. <u>ቤተ ደናግል</u>

- ይህ ቤተ መቅደስ ከቤተ ማሪያም በስተ ደቡብ የሚገኝ ቤተ መቅደስ ሲሆን ለቅድስት አንስት መታሰቢያ የተሰራ ነው ፡፡

7. ቤተ አማኑኤል

- ይህ ቤተ መቅደስ 18 በ12 በ12 ሜትር ይዘት ያለው ቤተክርስቲያን ሲሆን ከአለት የተፈለፈለ የላሊበላ ውቅር ቤተክርስቲያ ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ አራት የአለት አምዶች ይገኛሉ። ቤተ ክርስቲያን ሦስት የመግቢያ በሮች አሉት። የበሮቹ ሳንቃዎች 800 አመት የሞላቸው፣ ከእንጨት የተጠረቡና እስካሁን ብዙ ጉዳት ያልደረሰባቸው ናቸው።

8. ቤተ መርቆሬዎስ፡-

- ይህ ቤተ መቅደስ ከቤተ አማኑኤል ንፅፅር ነው 18 ምስልዎች (አፅማድ) አሉት።።

9. ቤተ ሊባኖስ

- ይህ ቤተ መቅደስ ከላይ ከጣርያው የተያያዘውም መሬቱን እና ገደሉን ተሸክሞት የሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ነው።።

10. ቤተ ገብርኤል

- ይህ ቤተ መቅደስ በሦስት ከፍል በአለመ መላእክት ምሳሌ ሰርቶታል።። እነሱም እዮር፤ ራማ፤ ኤረት በመባል ይታወቃሉ።። የዚህ ቤተ መንግስተ በር ግን በየት እንደሆነ አይታወቅም።። አገልግሎት የሚሰጠው በመሰላል (በድልድይ) ነው።።

11. ቤተ ጊዮርጊስ

- ይህ ቤተ መቅደስ የተሰራው በኖህ መርከብ ምሳሌ ነው የህንፃው ቁመት 12 ሜትር ከ16 ሳንቲ ሜትር ሲሆን የመቅደሱ የውስጥ ቁመትም 10 ሜትር ከ99 ሳ.ሜ ነው ይህ ቤተ መቅደስ ጣሪያው ሲታይ የመስቀል ቅርፅ ያለበት ሲሆን ራሱን ችሎ ከአንድ ወጥ የአለት ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሰራ ነው።።

4.2. ግሸን ደብረ ከርቤ

- ግሸን ደብረ ከርቤ ቤተ ክርስቲያን ከደሴ ከተማ 82 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በወሎ በአባሰል ወረዳ ውስጥ በአይቅና በመቅደላ ፣ በደላንታና በየእጁ መሀከል በበሸሎ ወንዝ አዋሳኝ ከፍተኛ በሆነ ተራራ ላይ የምትገኝ ገዳም ናት።። የበሸሎ ወንዝ ተሻግሮ ሰማይ ጥግ የደረሱ የሚስሉ ተራራዎችን ወጥቶ በስተ መጨረሻ መግቢያ አንድ በር ብቻ የሆነ ከተራራው አናት ላይ በሚገኝ ስፍራ ላይ በመቤታችን

ቅድስት ድንግል ማሪያም ስም የታነፀና ግማደ መስቀሉ የሚገኝበት የእግዚአብሔር አብ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡

- ግሸን ይህንን የአሁኑን መጠሪያ ስም ከማግኘቱ በፊት በተለያዩ ስሞች ትታወቅ ነበር፡፡
- በመጀመሪያ በአፄ ድልናኦድ ዘመነ መንግስት 866 ዓ.ም ሀይቅ ደብረ እስጢፋኖስ በተመሰረተ ጊዜ ሀይቅ ደብረ ነጎድጓድ ተብሎ ሲሰየም ግሸንን በሀይቅ ግዛት ስር ስለነበረች ስሟ ደብረ ነጎድጓድ ተባለች፡፡ ከዚህም በኋላ በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግስት ይኸውም ንጉስ ከቋጥኝ ድንጋይ ፈልፍሎ የሰራው ቤተ መቅደስ በእግዚአብሔር አብ ስም ይጠራ ስለነበር ግሸንም ደብር እግዚአብሔር ተብላ መጠራት ጀመረች፡፡ ነገር ግን በዚሁ ስም መጠራት ብዙ ሳትቆይ ነግስታቱ በብዛት የማፀኑባት ስለነብር ደብረ ነገስት ተብላ መጠራት ጀመረች፡፡ እንደገናም በ1446 ዓ.ም ኢትዮጲያዊው ፈላስፋ እየተባለ በሚጠራው አፄ ዘረያቆብ ዘመነ መንግስት ግማደ መስቀሉ መጥቶ በዚህ ቅዱስ ስፍራ ሲያርፍ ደብረ በገስት መባሏ ቀርቶ ደብር ከርቤ ተባለች፡፡
- አጼ ዘረያቆብም ግማደ መስቀሉን ሰሸክመው እየገሰገሱ ከብዙ ድካምና ፍለጋ በኋላ ወደ ተራራዋ በመድረሳቸው ጌሰ (ጌሠ) ገሰገሰ የሚለውን ቃል ከግዕዝ በመውሰድ ሲጠቀሙበት ከጊዜ በኋላ ግሸን የሚለው ቃል በህዝቡ እየተለመደ በመምጣቱ ግሸን ደብረ ከርቤ እየረባለች በመጠራት ላይ ትገኛለች፡፡
- የአካባቢውን ስም አንድ አባት ፍቃደ ክርስቶስ የሚባለ መንፈሳዊና መናኝ አባት ሁለት ፅላቶችን አሸክመው በሸለሞ ወንዝን ተሻግረው አቀበቱን ወጥተው ለመስቀለኛው አንባጥግ ሲደርሱ ወደ አንባው ጫፍ ለመውጣት መወጣጫ (ሰርጥ)ሲፈልጉ የአምባው ዙሪያ በገደሉ ላይ ንብ ሰፍሮ የማሩ ሰፈፍ ጨረቃ መስሎ በማየታቸው የአካባቢውንና የእግዚአየብሔርን የተፈጥሮ ስጦታ ሲያደንቁ ይህስ አምባ አሰል ነው ይህስ አምባ አሰል ነው በማለት ተናግረዋል አሰል የሚለው ቃል በአረብኛ ቋንቋ ማር ማለት ሲሆን ሙሉ ትርጉሙ የማር አምባ ማለት ነው፡፡ ከዚያን ዘመን ጀምሮ የግሸን ማሪያም አካባቢ ወረዳ አባሰል ተብሎ በመጠራት ላይ ይገኛል፡፡

4.3. ብልብላ ጊዮርጊስ

- ይህ ደብር በወሎ በላስታ አውራጃ በቡግና ወረዳ የሚገኝ አስደናቂ ደብር ነው። ወደዚህ ደብር ለመውጣት ከ15-25 ደቂቃ የሚወስድ ዳገት ይገኛል ቀደም ሲል የዚህ ቦታ ስም መካነ ሎዛ ይባል ነበር። መካነ ሎዛ ማለትም የረድኤትና የበረከት ቦታ ማለት ነው።በዚህም ቦታ ዘጠኙ ቅዱሳን መጥተው ለ40 ቀን ፀሎት አድርሰውበታል። ፡ከነሱም በፊት እመቤታችን በስደቷ ወቅት አርፋበታለች።በኋላም ጌታችን በእለተ ዓርብ ሲሰቀል ከጎኑ የፈሰሰው ደሙን መላእኩ ቅዱስ ኡራኤል በብርሃን ዕዋ ተቀብሎ ይህንን ቦታ ረጭቶታል።
- ከዚህ በኋላ በ484 ዓ.ም የነገሱት አፄ ካሌብ ፈንሃል የተባለው አይሁዳዊ ሀገረ ናግራንን ባጠፋ ጊዜ ንጉሱ ወደ ናግራን ዘምተው አይሁዳዊውን ድል አድርገው ሲመለሱ መፀሐፍተ ብሉያት እና የተለያዩ ታቦታትን ታቦተ እግዚአብሔር አብን ፣ ታቦተ አርባእቱ እንስሳ፣ ታቦተ ማሪያምን፣ ታቦተ ጊዮርጊስን፣ ታቦተ ሚካኤልን፣ ታቦተ ቂረቄስን ይዘው ሲመለሱ ደብረ ሩሃ በተባለ ቦታ ላሊበላ የሚያንፃቸውን አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ ታንፀው ስለ ታያቸው ሲገሰግሱ ሩሃ ከተባለው ቦታ በሰላም ደረሱ እንደደረሱም ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ለንጉሱ ተገልፆ እንዲህ አላቸው ወዳጄ ካሌብ ሆይ እየተቻኮልክ ወደዚህ ብትመጣም አንተ የምታንፃቸው ቤተ መቅደሶች ከዚህ አይደሉም በዚህ በሩሃ ቤተ ክርስቲያን የሚያንፀው ግና አልተወለደም። አንተ ቤተ መቅደሴን የምታንፅበት ቦታ ግን አምደ ብርሃን ይመራሃል አለው። በዚህ ጊዜ አፄ ካሌብ ይህ ምስጢር በተገለፀላቸው ከ14 ቦታ ላይ ወርቅ ቀብረው ሲመለሱ አምደ ብርሃን የመራቸው ብግና መካለ ሎዛ ሲደርሱ አምደ ብርሃኑ ቆመ እንደ ምንጣፍም ተነጠፈ በዚህ ጊዜ ፈጣሪዬ በዚህ ቦታ አንፅ ሲለኝ ነው ብለው መጀመሪያ ቤተ ጊዮርጊስን ከቆጥኝ ድንጋይ አነፁና ከዚያም በመቀጠል ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ካነፁ እና ታቦታቱን ካስገቡ በኋላ ቅዳሴ ቤታቸውን በመካነ ሎዛ በቤተ ጊዮርጊስ ውስጥ ህዳር 7 518ዓ.ም አክብረው ሲፈፅሙ ስፍር ቁጥር የሌለው ንብ በጥቶ ከቤተ መቅደሱ ገብቶ ሰፈረ። በማግስቱም ህዳር 8 ቤተ መቅደሱ ፣በማር ተጥለጥቆ ተገኝቶል ይህን ማር ህዝብ ለበረከት እያለ ወደየ ቤቱ በሚወስድበት ጊዜ የተለያየ ደዌ ያለባቸው ሁሉ ከህመማቸው ተፈውሰዋል።
- በኋላም አፄ ካሌብ መናኔ መንግስ መሆን ይህን ሃላፊ አለም ትተው ገዳም በመግባት መንኩሰዋል። ከዚህ በኋላ በ534 ዓ.ም የነገሱት የአፄ ካሌብ የልጅ ልጅ የአፄ ገ/መስቀል ልጅ ቆስጠጢኖስ ስመ ንግስና ይሰሐቅ የተባለው ንጉስ እንደነገሰ ወደ

ቡግና መካነ ሎዛ ደረሰ ከዚያም የአባቱ አባት አያቱ አፄ ካሌብ ካነፀው ቤተ መቅደስ መካነ ሎዛ እንደደረሰ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ ሰገደ። ሰግዶም እንደቆመ በተአምራት አስደናቂ የሆነ ነበልባል (በእለት ነበልባል) ከቤተ መቅደሱ በር ሲንቦገቦግ ከነሰራዊቱ ቆሞ ተመለከተ።

- ንጉሱም ከነሰራዊቱ እየተመለከተ ሲደነቁ ስፍር ቁጥር የሌለው ንብ ከቤተ ምቅደስ ወጥቶ ንጉሱ ያረፈበት ድንኳን ውስጥ ሰፈረ ይህም ድንኳን በማር ተሞልቶ ተገኘ በኋላም ይህን ሁሉ ስራዊት ተመልሶ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ። በዚህ ሁኔታ ክምሽቱ 3 ሰዓት ሲሆን የቤተ ምቅደሱ አፀድ እንደ እሳት እየነደደ ነበላባሉን ከሰማይ እንደደረሰ መስሎ ሲንበለበል ለሊቱን ሙሉ አደረ በዚህም ምክንያት የእሳት ነበልባል ከቦት ስለታየ መካነ ነበልባል ዘቤተ ጊዮርጊስ ተብሎ ተሰየመ። ከጊዜ በኋላ አማርኛው እየተለወጠ ነበልባል የነበረው ብልብላ የሚል ስም ሊይዝ ችሎል ፡

4.4. ይምርሃነ ክርስቶስ ታሪክ

- ንጉስ ይምርሃነ ክርስቶስ ከሦስቱ የኢትዮጲያ ወንድማማቾች ነገስታት መካከል የግርማ ስዩም ልጅ ነው ። እነዚህም ወንድማማቾች ነገስታት የሚባሉት 1ተኛ ግርማ ስዩም 2ተኛ ዣን ስዩም 3ተኛ ጠንጠውድም ስዩም ናቸው። የይምርሃነ ክርስቶስ የላሊበላ አጎት ልጅ ነው። ይምርሃነ ክርስቶስ ከላሊበላ በፊት የነገሰ ንጉስ ነው። የንግስና ዘመኑም 40 ዓመት ነው። ክህነትን ከንግስና ጋር አስተባብሮ የያዘ አስተዋይ ንጉስ ነው ።
- ከቅድስናውም የተነሳ ቅዳሴ ገብቶ ሲቀድስ ሰማያዊ መና ወወይን ከነፅዋው የወረደለት ታላቅ ምስጉን እውነተኛ ንጉስ ነው። የቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ ህንፃ ቤተ ክርስቲያ የተነፃው ጥቁርና አለታማ ከሆነ ተራራ ከታችኛው ክፍል ላይ በሚገኝ እጅግ ሰፊና ትልቅ በሆነ ውግረ ስሂን በተባለ ዋሻ ውስጥ ነው። ይህን አስደናቂ ህንፃ ያነፀው እራሱ ይምርሃነ ክርስቶስ ነው። የዚህ ፃዲቅ ንጉስ ይምርሃነ ክርስቶስ ባአለ እረፍት የሚከበረው ጥቅምት 19 ቀን ነው።

ምዕራፍ አምስት

ጎጃምና ባህርዳርና ዙሪያዋ የሚገኙ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያት ማሳያ

5.1. ጣና ሀይቅ ገዳማት

- የጣና ሀይቅ በኢትዮጲያ ውስጥ ከሚገኙ ሀይቆች ሁሉ በትልቅነቱ ቀዳማዊ ስፍራ የያዘ ነው፡፡ ጣና ሀይቅ 3600 (ሦስት ሺህ ስድስት መቶ) እስኩኤር ኪ.ሜ በአጠቃላይ ስፋት ሲኖረውም አቀማመጡ ስሜን ወደ ደቡብ 75 ኪሜ ሲሆን ከምስራቅ ወደ ምዕራብ 60 ኪሜ ያለው ነው፡፡ የጣና ሀይቅ ከባህር ወለል በላይ 1830 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም በጣና ሀይቅ በመሀሉና በባህሩ ዳርቻ በአጠቃላይ ከ30 በላይ የሚሆኑ የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሃብት የሆኑ በብዙ ቢሊዮን ከሚገመቱ ቅርሳቸው ጋር ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ገዳማት መሀከል፦

1. **ደብር ማርያም፦** ከጣና ሀይቅ በደቡብ ምስራቃዊ ጫፍ በኩል የምትገኝ የረጅም ጊዜ እድሜ ያላት አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ይህቺ ገዳም ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኟት አብነ ታዲዮስ ይባላሉ እኚሁ አባት ወደደሴቷ በደረሱ ጊዜ የጣናን ሀይቅ ለሁለት ከፍለው ያለምንም ችግር እስራኤላውያን ባህረ ኤርትራን እንደተሻገሩ ሁሉ እኚህም አባት በየብስ ላይ ተራምደው ተሻግረዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቷ የታነፀችው በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት ሲሆን ለሁለተኛ ጊዜ በአፄ ተዎድሮስ ዘመነ መንግስት ተሰርታለች፡፡ የዚች ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈነ ሲሆን በአጠቃላይ አካባቢው የተፈጥሮ ውበት ያለው ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኗም በተጎሳቆለ ሁኔታ ላይ የምትገኝ ቢሆንም ታሪካዊና ጥንታውያን የግርግዳ ስዕሎች ረጅም እድሜ ያላቸው የብራና መፀሐፍት ታላላቅ ጥበባዊ ስራዎች እና ንዋየ ቅዱሳት የሚገኙባት በመሆኗ የቱሪስት መስብ ናት፡፡
2. **ክብራን ገብርኤል፦** በጣና ሀይቅ ደቡባዊ ዳርቻ ላይ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ታላቅ ገዳም ነው፡፡ ይህ ገዳም በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት የተተከለ ሲሆን ገዳሙን የገደሙት አባ ዘዮሐንስ ናቸው፡፡

3. **ውራ ኪዳነ ምህረት፦** ከባህር ዳር ሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ በአንድ ጐኑ ከየብስ ጋር በሌላ ጐኑ ከሐይቁ ጋር የተገናኙ በተፈጥሮ ልምላሜው ማራኪ ደሴት በሆነ ላይ የምትገኝ ክብ ቅርፅ የሆነች እና የሣር ክዳን ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ የተመሰረተችውም በ፲፬ኛው ክ/ዘመን ቢሆንም በገዳምነት የፀናችው በአፄ አድያም ሰገድ እየሱስ ዘመነ መንግስት ነው፡፡
4. **መሐል ዘጌ ጊዮርጊስ፡-** ይህ ቤተ ክርስቲያን በ፲፪ኛው ክ/ዘመን ሲሆን የመሰረቱትም አብነ በትሪ ማሪያም የተባሉ ፃዲቅ አባት ናቸው፡፡
5. **አዝዋ ማርያም፡-** በዚች ገዳም ውስጥ የስነ ጥበብ ሥራ በሚያስደንግ ሁኔታ የሚታይበት ገዳም ነው፡፤
6. **ደጋ እስጢፋኖስ፡-**
7. **ጣና ቂርቆስ፡-** የትውፊት ማህደር እና የቅርስ ሙዝየም የሆነ ታላቅ ገዳም ነው፡
8. **ክርስቶስ ሳምራ፡-** ደብረ ጓንጉት በጣና ሐይቅ ዳርቻ ከጉማራ ወንዝ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ላይ ትገኛለች፡፡

5.2. <u>መርጡለ ማርያም</u>

- ኢትዮጲያ ከምትታወቅባቸው እና ከምትደነቅባቸው ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል መርጡለ ማርያም አንዷ ናት፡፡
- መርጡለ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው በምስራቅ ጐጃም ዞን በእናብሴ ሣር ምድር ወረዳ መርጡለ ማርያም በሚባል የገጠር ከተማ ውስጥ ነው፡፡
- በዚህም ጥንታውያን ስፍራ በቀድሞ አጠራር በጐጃም ክ/ሀገር በምጠ አውራጃ በእናብሴ ወረዳ ከአባይ ወንዝ በግምት ፴፭ (35) ኪ.ሜ ርቃ በወይና ደጋ የአየር ንብረት ክልል የተቆረቆረችው ከዘመን ብዛት የረኃሳ የስም መለዋወጥ የረሰጣት ጥንታውቷ ቦታ መርጡለ ማርያም ናት፡፡
- ከሁለተኛው ሺህ አመተ ዓለም ጀምሮ ነገደ ካም የኪሽ ልጆች አባይን ተከትለው ወደ ኢትዮጲያ በመግባት በመርጡለ ለማርያም አካባቢ መንደራቸውን መሰረተው ከ፲፯፻፵ (1740) አመታት ያላነሰ ጊዜ እግዚአብሔርን ከህግ ልቡና ሲያመልኩ ኖረዋል፡፡
- ወደዚህ ቦታ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት ችግር ሣይደርስባቸው በሰላም ስለኖሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ቦታውን ሀገረ ሰላም ብለውታል፡፡ በማያያዝም ቀዳማዊ

ምኒልክ በኢትዮጲያ በነገሰ ጊዜ ከእየሩሳሌም አብረው የተላኩትን ነገደ እስራኤል በየሙያቸው ደልድሎ በየግዛት ሀገሩ ላካቸው፡፡

- በዚህ ጊዜ ፈረሰኞችን በአስተዳደር ሌዋውያን ከህናትን እና ጠበብተ እስራኤልን የተለያዩ የማምረቻ መሳሪያዎችን ከማምረት በተጨማሪ ምኩራብ አሪትን እንዲሰሩ እና እንዲያገለግሉ መደባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ጐጃምን እንዲያስተዳድር ከሌዋውያን ካህናት ጋር ወደ ጐጃም የተላከው አለቃ ኤፍሬም የተባለ ነበር፡፡
- ኤፍሬም ከሰሜን ኢትዮጲያ ወደ ጐጃም ምድር እንደገባ ርዕሰ ከተማውን ነገደ ካም ቀደም ሲል በፍሬው ውበት በነበረችው ሀገር ሰላም (መርጡለ ማርያም) አደረገ፡፡
- ጠበብተ እስራኤል እና ሌዋውያን ደግሞ የኦሪትን ግህና ሥርዓት በሀገረ ሰላም (መርጡለ ማርያም) ቤተ ምኩራብ እንዲሰሩ አደረገ፡፡ ቤተ ምኩራቡን ሰርተው እንደጨረሱ የቦታውን ስም ጽርሐ አርያም ብለው ሰይመውታል፡፡
- ኪዚህ ዘመን ጀምሮ ህገ ኢሪትን በመፈፀም የእግዚአብሔር ስም ሲያመሰግኑ ሲያገለግሉ እስከ ዘመነ ሀዲስ (አብርሀ እና አፅባሀ) እስከነገሱበት ዘመን ደርሰዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በቁስጥንጥንያ መንግስት ቁንጠ በኢትዮጲያ ደግሞ አብርሃ እና አፅባሃ ነግሰው በነበረነት 330 ዓ.ም በከሳቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ትምህርት በአክሱም ጽዮን በተድበበ ማርያም በመርጡለ ማትያም እንዲሁም በጣና ቂርቆስ ቦታዎች ህገ ኦሪት ሲፈፀምባቸው በነበሩት የኦሪት ምኩራባት ላይ ሀዲስ ወንጌል ተሰበክ፡፡
- የመጀመሪያዋ የኢትዮጲያ ቤተ ክርስቲያን መሰረት ንዑዳን እና ክቡራን በሆነ አብርሃ ወአፅባሀ እና አቡነ ሰላም ካሳቴ ብርሃን ቡራኬ ተጣለ፡፡ ለዚህም ፈለገ ግዮን አብርሃ ወአፅበሃ ዘምሰለ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ወነፅኹ ምጽፈ ጐጃም ወሀነፅዎ ለመርጡለማርያም በወርቅ ወበእንቁ በማለት ገድለ አብርሃ ወአፅባሃ እንዲሁም ገድለ አቡነ ሰላም ጣስለዳል፡፡መፃሕፍቱም በአክሱም ጽዮን በመርጡለ ማርያም ይገኛል፡
- ከዚህም በመቀጠል በ333 ዓ.ም ጥር 21 ቀን በጳጳሲ አብነ ሰላም ከሣቴ ብርሃን ቤተ ክርስቲያን ተባርኮ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ በዚህ ጊዜ አቡነ ሰላም ከሳጤ ብርሃን ፅርሃ ያለው መርጡለ አርያም ያለውን ማርያም በማለት የማርያም አዳራሽ የተሰኘውን ስም ሰይመዋታል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መርጡለማርያም የሚለው እስከ አሁን መጠሪዋ ሆኖ ይገኛል፡፡

5.3. ደብረ ወርቅ ማርያም

- ደብረ ወርቅ ማሪያም ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን በሞጠ ባህርዳር በሚወስደው 290 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ደብር ናት።።(የእናርጅ እናውጋ ወረዳ ማዕከል በሆነችው ደብረ ወርቅ ከተማ ውስጥ ትገኛለች።። ይህቹ ቤተ ክርስቲያን ከከተማዋ በስተ ምስራቅ በኩል መሶበ ወርቅ በመሰለው ተራራ ቅንጮ ላይ ህሊናን በሚመስጥ ሁኔታ ቅልጭ ብላ ትገኛለች።። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለመግባት ከመንገዱ እስከ ተራራው ጫፍ 69 ደረጃዎች ይገኛሉ።።
- ደብር ወርቅ በዘመነ ኦሪት በኢትዮጲያ ውስጥ ከነበሩት ምኩራባት አንዷ በመሆኗ ህገ ኦሪት ሲፈፀምባት የነበረች ቦታ ናት።። አብርሃ ወአፅባሃ ከአብነ ሰላም ከሣቴ ብርሃን ጋር የክርስትና ሃይማኖትን ለማስተማር በመላው ኢትዮጲያ ሊዘዋወሩ ከመርጡለማርያም ቀጥለው ወደ ደብረ ወርቅ ነበር ያመሩት (የሃዱት አብርሃ ወአፅብሃ መርጡለ ማርያም ካነፁ በኋላ ደብረ ወርቅን ለመቀጠል ሲያስቡ ግለ አረፍተ ዘመን ስለገታቸው አደራውን ለልጃቸው ለአስፍሐ ትተው አረፉ።። ንጉሰ አስፍሐም አደራውን ጠብቆ በ፲፱፱ዎቹ ዓ.ም ውስጥ (360) ቤተ ክርስቲያንኗን በወርቅ አስጊጦ በመስራት ታቦተ ማርያም እንድትገባ አድርጓል።። ደብረ ወርቅ የሚለውፈንም ስም የሰየመው ይህ ንጉስ አስፍሐ ነው።። ቤተ ክርስቲያኗም ለመስራት ሲመጣ በዚች ቦታ ላይ የወርቅ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተተክሎ በራዕይ ስለአየ ከዚህ በመነሳት ደብረ ወርቅ ብሏታል።።
- ደብር ወርቅ ከመርጡለ ማርያም ጋር ለአካባቢው የክርስትና ማዕከል በመሆን ብዙ ሊቃውንትንና ምዕመናንን ያፈራች ጥንታዊት ቦታ ናት።። ደብር ወርቅ ገዳም ከተመሰረተች ከ፭፻ (500) አመታት በኋላ ዮዲት ጉዲት ክርስትናን ከኢትዮጲያ ለመጥፋት በተነሳች ጊዜ ጉዳት ከደረሰባቸው አድባራት አንዷ ናት።።
- በ፲፫ኛው (13ኛው) ክ/ዘመን አባ ሰርጹጥሮስ የተባሉ አባት ከእነብሴ አካባቢ የተነሱ ነምስራቅ ጐጃምም በዘመነ ዮዲት ተዳክሞ የነበረውን የክርስትና ትምህርትን በይበልጥ አሰፋፍተዋል።።የደብረ ወርቅ ዝናም እየገነነ የመጣበት ጊዜ ቢሆን በጊዜው የነበሩት አፄ ዳዊት አባ ሠርፀ ጹጥሮስን አስጠርተው ደብረ ወርቅ እንደገና እንድትታነፅ እና ከመቋቋ እንድትወጣ አድርገዋል።።
- አፄ ዘርዓ ያዕቆብም በዘመናቸው ከአረማውያን ጋር ሲዋጉ ጦር ቢያይልባቸው የአባ ሰርፀጹጥሮስን ዝና ስምተው ስለነበር እንዲፀልዩላቸው ላኩባቸው እግዚአብሔርም የእንሂን አባት ፀሎት ተቀብሎ ጠላታቸውን ድል በማድረጋቸው ከድል መልስ የጦር

ልብሳቸውን በሙል ለደብር ወርቅ ማርያም አበርክተዋል፡፡ በአፄ ዳዊት ዘመን በጭቃ የተሰራችው ደብረወርቅ የግራኝ መሀመድ የመከራ ዘመንን አልፋ በአፄ ገላውዲያው ጊዜ በኖራ ታድሳለች፡፡

ምዕራፍ ስድስት

ሸዋ እና ዙሪያዋ የሚገኙ ጥንታውያ አብያተ ክርስቲያት ማሳያ

6.1. ደብረ ብርሃን ሥላሴ

- ይህ ቤተክርስቲያን በ16ኛው ክ.ዘ የነገሠው የአፄ ፋሲል የልጅ ልጅ አለም ሰገድ(አድያም ሰገድ) ኢያሱ በኖህ መርከብ አምሳያ ጎንደር ከተማ ላይ ያሰራው ቤተክስቲያን ነው ስሙም ደብረ ብርሃን ሥላሴ ነው ይህ ዓለም የሰገደለት ንጉሥ ክህነትን እና ንግሥናን ሁለቱን ስልጣን በማጣመር ኢትዮጵያን ገዝቷል ቤተመቅደስ ገብቶ ካህን ሁኖ ይቀድሳል ቤተመንግስት ደሞ ንጉሥ ሁኖ ሀገር ይመራል አንዲያውም ይሄ ንጉሥ አክሱም ጽዮን ማርያም በመሄድ ታቦተ ጽዮንን ተሸክሞ ንግሥና እንዳከበረ ይነገርለታል።ልብ በሉ በመፅሐፍ ቅዱስ በጣም ገናና ከሆኑት የእስራኤል ነጉሦች መካከል ንጉሥ ዳዊትና ጠቢቡ ሰለሞንን እንኳ የኢትዮጵያውን ንጉሥ ቂረኛው እያሱን ያክል ስልጣን አልነበራቸውም ለምን ዳዊትና ልጁ ሰለሞን የክህነት ስልጣን አልነበራቸውም ነበር የክህነቱን ቦታ የሚያገለግሉ የሌዊ ነገዶች ብቻ ናቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት ግን ከንጉሥነት አልፎ ካህንም ነበሩ ለዛ ነው የውጭ ሀገር ታሪክ ጽሐፊዎች የኢትዮጵያን ነገሥታት ሲጠሯቸው "prester john" ነው ሚሏቸው ትርጉሙም "ቄሱ ንጉስ"ማለት ነው ።ነገር ግን በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ኢትዮጵያ የተዳከመችበት ዘመን ነበረና ከግብፅና ሱዳን የመጡ አክራሪ ደርቡሾች በቀላሉ ጎንደርን በወረሩ ግዜ 43ቱን ጥንታዊ ቤተክርስቲያንን አቃጥለው ወደ 44ተኛው ወደዚሁ ስላሜ ቤተክርስቲያን ሲመጡ ከየት እንደመጣ የማይታወቅ ነጭ ንብ ድርቡሾችን እየነደፈ አባረራቸው ቤተክርስቲያኑም ለወሬ ነጋሪት ለታሪክ ምስክርነት ብቻውን ሳይቃጠል ቀረ።

6.2. ቅድስት ክርስቶስ ሰምራ

- ቡልጋ ሀረገ ማርያም፣ ኮዬ፣ ስኮር፣ ንፋስ አምባ የሚባሉ የገጠር ከተሞችን አልፈን ሾላ ገበያ ዋና እንደርሳለን። ከመኪናችን እንደወረድን ጥቂት መንደሮችን አልፈን በረጅም ርቀት አሻግረን ስንመለከት ጉብ ባለች መጠነኛ ቦታ ላይ ችምችም ያለ አጸድ ሲመለከቱ እና እይተጠጉ ሲሄዱ ከ 800 ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠሩ በኢትዮጵያዊት ጻድቅ የእምነት ሴት አርበኛ ጻድቅ ክርስቶስ ሠምራ በእጇ የተተከለ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ቅርስ የተጋድሎ ባዕቷንና አሁን ታቦተ ህጉ ያለበትን ትንሽ መቃኞ ይገኛል። የገዳሟም ስም ጌዬ ገዳም ሲሆን ዕድሜ ጠገብ ባለታሪክም ነው።

6.3. ደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም

- የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃማኖት አንድነት ገዳም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ከአዲስ አበባ ወደ ጎንደር- ጎጃም መውጫ በ104 ኪሎ ሜትር ርቀት፤ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ 4.5 ኪሎ ሜትር ተገንጥሎ የሚገኝ የአንድነት ገዳም ነው።
- ገዳሙ በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ1296 ዓ.ም የተቆረቆረ ሲሆን፤ 710 ዓመታትን አስቆጥሯል። በገዳሙ አስተዳደር ሥር ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በተጨማሪ የቅዱስ አማኑኤል እና የቅዱስ ፊልጶስ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ።
- በገዳሙ ውስጥ የሚጎበኙ የተለያዩ የነገሥታት ሥጦታዎች፤ ቅዱሳት መጻሕፍት፤ ንዋየ ቅድሳት፤ የቅዱሳን አጽም፤ ፈውስ የሚገኝባቸው የጸበል ቦታዎችም ይገኛሉ።
- ደብረ ሊባኖስ ማለት የሊባኖስ ተራራ ማለት ነው። ጻድቁ አቡነ ሊባኖስ የተባሉት ሮማዊ አባት ለአርባ ዓመታት የጸለዩበት፤ ብዙ ገቢረ ተአምራት ያደረጉበት፤ ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኙበት ነው። ደብረ ሊባኖስ "ትትሌአል ወትከብር እምነ ኩሎን አድባራት ወገዳማት እሞን ለአሀጉር፤ ከአድባራትና ገዳማት ትከብራለች፤ ከፍ ከፍም ትላለች፤ ለሀገራትም እናት ትባላለች" የተባለላት የበረከት ቦታ ነች።
- አባ ሊባኖስ በጌታ የተወደደውንና የቅዱሳን ከተማ ደብረ ሊባኖስን በጣም ይወዱት ነበር። ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ይህ ቦታ ከአንተ በኋላ ለሚመጣው ለተክለ ሃይማኖት ነውና አንተ ወደ ትግራይ ሀገር ሒድ፤ እድል ፈንታህ በዚያ ነው አላቸው። እርሳቸውም አርባ ዓመታት የደከምኩበት ለከንቱ ነውን? አሉት ቅዱሳን አጽንኦተ በዓት ይወዳሉና። መልአኩም ስለ ድካምህ ይህ ቦታ ደብረ ሊባኖስ ይባላል እንጂ ደብረ ተክለ ሃይማኖት አይባልም አላቸው። እሳቸውም ፈቃድህ ይሁን

ብለው ወደ ትግራይ ሀገር ሔዱ፡፡ እስከ ዛሬም ድረስ ደብረ ሊባኖስ እየተባለ ይጠራል፤ ስመ ተፋልሶም አላገኘውም፡፡

- የደብረ ሊባኖስ ገዳም ደብረ ሊባኖስ ከሚለው መጠሪያ ውጭ ሌሎች ስያሜዎችን አለት የመጀመሪያው ምድረ ግራርያ ይባላል፡፡ግራሪያ የሚለውን ስያሜ የሰጠችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ከወዳጇ ከጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ ምድረ ግብጽ ስትሰደድ በኢትዮጵያ ውስጥ ከቆየችባቸው ቦታዎች አንዱ ይህ ቅዱስ ቦታ ነው፡፡ ለአንድ ሳምንት ቆይታ አድርጋ የቦታውን ስም ምድረ ግራሪያ ስትል ሰይማዋለች፡፡ ግራሪያ ማለት‹‹ ኩሉ ይገርር ለቱ፤ ሁሉ ይገዛላታል›› ማለት ነው፡፡ አንድም ግራር በቁሙ ለሁሉ ጥላ፤ መሰብሰቢያ እንደሆነ ደብረ ሊባኖስም የሁሉ ጥላ መሰብሰቢያ ነውና ምድረ ግራሪያ ተብሏል፡፡
- ሁለተኛው ስያሜው ደብረ አስቦ ይባላል፡፡ ደብረ አስቦ ማለት የዋጋ ተራራ ማለት ነው፡፡ የሰየመውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ አባታችን ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዚህ ቅዱስ ሥፍራ ሃያ ዘጠኝ ዓመታት ከጸለዩ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል፡፡ ቦታውንም ደብረ አስቦ፤ የድካምህ ዋጋ፤ የስምህ መጠሪያ ይሁንልህ በማለት ሰይሞታል፡፡
- ሦስተኛው የደብረ ሊባኖስ መጠሪያ ኤላም ይባላል፡፡ ኤላም ማለት የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ ማለት ነው፡፡ ይህ ቦታ የአባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት አጽም ለአርባ ዓመታት የቆየበት ቅዱስ ሥፍራ ነው፡፡ ስያሜውም የአቡነ ዮሐንስ ከማ ነው፡ ፡ ዮሐንስ ከማ የጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመንፈስ ልጅ ናቸው፡፡ ኤላም የበረከት ቦታ፤ የሰላም ሠፈር ነው፡፡ የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተሰውሮ ይገኝበታል፡፡
- አራተኛው የደብረ ሊባኖስ መጠሪያ ዜጋመል ነው፡፡ዜጋዎ አመል ማለት የአየር ንብረቱ የተመቸ፤ የሚያስደስት፤ ተስማሚና ለኑሮ የሚመች ማለት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ዜጋዎ አመል ተብሏል፡፡
- የደብረ ሊባኖስ ገዳም ከሐዲስ ኪዳን መጀመርያ ላይ አንስቶ ድንቅ ድንቅ ተአምራት የሚደረግበት ታላቅና ታሪካዊ ገዳም ነው፡፡ ይህ ገዳም ከተመሠረተ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በውስጡ የሚደረገው ተአምር እፁብና ድንቅ ነው፡፡ ዕውራን ዓይናቸው

ይበራል፣ ደንቆሮዎች ጆሯቸው ይሰማል፣ በአልጋ ተይዘው የመጡ በሽኾች ድነው በእግራቸው ይሄዳሉ፡፡

- በአባታችን በአቡነ ተክለ ሃይማኖት በ1267 ዓ.ም ወደዚህ ገዳም በመምጣት ገዳሙን ገድመው ለሃያ ዘጠኝ ዓመታት በደብረ አስቦ ዋሻ በተጋድሎ ኖረዋል፡፡ ነሐሴ 24 ቀን በ1296 ዓ.ም በተወለዱ በ99 ዓመት ከአስር ወር ከአስር ቀን ሲሆናቸው አረፉ፡ ፡ ጌታችንም እስከ አሥር ትውልድ ድረስ እንደሚምርላቸውና ሌላም ብዙ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል፡፡ ባረፉ በሃምሳ ሰባት ዓመታቸው በ1353 ዓ.ም አፅማቸው ከደብረ አስቦ ዋሻ ወደ ኤላም ፈልሷል፡፡ በዚያም ለአርባ ዓመት ከቆየ በኋላ አሁን ቤተክርስቲያኑ ወደ አለበት ቦታ ፈልሶ/ተዘዋውሮ/ በላዩ ቤተክርስቲያን ተሠርቶበታል፡፡ በመቀጠልም በመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው

ምዕራፍ ሰባት

ምዕራብና ምስራቅ ደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ጥንታውያን አድባት እና ገዳማት ማሳያ

7.1. ቁልቢ ገብርኤል

- ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ 461ኪ/ሜ ርቀት ላይ በምስራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጋራሙሉታ የሚገኝ ቤተክርስቲያን ነው። የዚህን ደብር አመሰራረት በተመለከተ በብዙ ሊቃውንት የሚተረከው የሚከተለው ነው።በዘጠነኛው መ/ክ/ዘ ዮዲት ጉዲት ተነስታ አብያተ ክርስቲያናትን ስትመዘብር፣ ክርስቲያኖችን ስትገድልና መጻሕፍትን ስትቆነጻጽል ንጉስ አንበሳ ውድም በአክሱምና በአካባቢዋ የነበሩ ታቦታትንና ንዋያትን ቅዱሳትን በመያዝ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ዝዋይ መጣ።
- ከ40 አመታት ስደት በኋላ አንበሳ ውድም ወደ አክሱም ሊመለስና የንዋያት ቅዱሳት ቆጠራ ሲደረግ ታቦተ ቅዱስ ገብርኤል በዝዋይ መቅረቱ ታወቀ። ከኤርትራ ደብረ ሲና ማርያም የመጡና አባ ሌዊ የተባሉ አባት ታቦቱን ለማምጣት ከንጉሱ አስፈቅደው ወደ ዝዋይ መጡ። አባ ሌዊ ከሰባት ቀን ሱባኤ በኋላ ታቦት ቅዱስ ገብርኤልን ይዘው ወደ አክሱም ሲጓዙ ቅዱስ ገብርኤል ተገልጦ "እኔ ወደ ማሳይህ ቦታ ታቦቱን ይዘህ ሂድ" አላቸው። አባ ሌዊም ታቦቱን ይዘው ተከተሉ። በመጨረሻም ቁልቢ ደረሱ። ለአባ ሌዊም የተፈቀደላቸው ቦታ ይሄ መሆኑን ታቦቱም በኋላ ዘመን ለህዝቡ ድንቅ ስራ እንደሚሰራ ቅዱስ ገብርኤል ነግሯቸው ተሰወረ።
- አባ ሌዊ በቦታው ለ130 ዓመታት ያህል አገልግለዋል በንጉሥ ግርማስዩም ዘመነ መንግስት ታኅሳስ 14 ቀን ዐርፈዋል። ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን ሲወርር ብዙ ካህናት ከሰሜን ኢትዮጵያ ታቦታችንንና ንዋያት ቅዱሳትን ይዘው ሲጓዙ ቁልቢ

ደረሱ። መልአክ ገነት ምብረቁ፤ መንሀር የማነ አብ ፥ አባ ተክስተ ስሉስ የተባሉ ካህናት ከተነጠፈ ድንጋይ ላይ የተጻፈ ነገር ያገኛሉ። ጽሑፉም ታቦተ ቅዱስ ገብርኤል በስውር መቀመጡን፥ ልዩ ልዩ ተአምራት እንደሚፈጸምበት፤ እንዴት አባ ሌዊ ታቦቱን ወደዚህ ቦታ እንደአመጡት የሚገልጽ ነበር።እርሱም ይህንን ታሪክ ይዘውት በነበረው መጽሐፍ ቀሌሜንጦስ ሕዳግ ላይ ጻፉት። ወደ ዝዋይ ደሴት ሲደርሱም መጽሐፍን በዚያ አኖሩት። ልዑል ራስ መኮንን ከዝዋይ ደሴት ቀሌሜንጦስን አስመጥተው ሲያነቡ የቁልቢ ገብርኤልን ታሪክ በማግኘታቸው የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ለማነጽ ተነሱ።

- ልዑል ራስ መኮንን በአካባቢው የአየር ንብረቱ ተማርከው በስስፍራው ቤት ሰርተው ነበር። ልዑል ራስ መኮንን ቁልቢ ገብርኤልን ከመትከላቸው በፊት ቦታው የአካባቢው ጎሳዎች የግጭት መነሀርያ ነበር ሰላምን በአካባቢው ከመሰረትህ በቦታው በስምህ ቤተክርስቲያንን እሰራለሁ ብለው እንደተነሳሱም ይነገራል።የተሳሉት በመፈጸሙ የቅዱስ ገብርኤል ታቦት የት እንዳለ ሲያፈላልጉ ቡልጋ ውስጥ ከአገሮጉጉ ካህናተ ሰማይ ጋር አባ ዱባለ የተባሉ ካህን ያስቀመጡትን ታቦተ ቅዱስ ገብርኤል መኖሩ ተነገራቸው። ልዑል ራስ መኮንን ለአባ ዱባለ መልዕክት ስለላኩባቸው ከሐገር በተላኩ ካህናት አማካኝነት የቅዱስ ገብርኤል ታቦት ላኩ።
- ልዑል ራስ መኮንንም ከነሰራዊታቸው ሸንኮራ ድረስ ሄደው ታቦቱን በመቀበል የካቲት 21 ቀን 1884 ዓ.ም ታቦቱ ቁልቢ ገባ። የመቃኛው ስራ በ1883 ዓ.ም ተጀምሮ ፍጻሜ አግኝቶ ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው ሐምሌ 19 ቀን በ1884 ዓ.ም ነው። የቤተክርስቲያኑ ስራ ተፈጽሞ በአቡነ ማትያስ ተባረከ። ቦታውን ከባለ አባቶች የገዙት በአርባ የቁም ከብት ነው። ራስ መኮንን መጋቢት ዘጠኝ ቀን 1889 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ እዚህ ቦታላይ በድንገት ስለታመሙ በዕለቱ ስጋ ወደሙ ተቀብለውበታል። በመጀመርያ ሲተከል በገጠር ቤተክርስቲያን ስራት ሲሆን በኋላ ግን በስዕለት ሰማኢነቱ በመላ ኢትዮጵያ እየታወቀ ስለመጣ ደብር ሆኗል።

7.2. <u>አዲስ አለም ማርያም</u>

- አዲስ ዓለም ርዕሰ አድባራት ደብረ ጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን በአፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት በ1894 የተመሰተችው።

- የአዲስ አለም ማርያም ታቦት አመጣጥ ከአክሱም ነዉ፡፡ ከእዉነተኛዪቱ የሙሴ ጽላት ጋር በአንድ ወቅት በአንድነት ይቀደስባቸዉ ነበር፡፡ ይህች ታቦት በንጉስ አብርሀ እና አጽብሀ ዘመነ መንግስት ወደ ሸዋ ምድር ክርስትናን ለማስፋፋት በተደረገዉ ጉዞ ከአክሱም ምድር ተንቀሳቅሳለች፡፡ ከዛም በጥፋት ዘመን ከ300 አመታት በላይ በዋሻ ተደብቃ ስትኖር እንደነበር በመጨረሻም በዳግማዊ አፄ ሚኒልክ ዘመነ መንግስት ወደ አዲስ አለም ምድር ተወስዳ በክብር ትገኛለች፡፡ ይህች ታቦት ባለችበት ስፍራ ተአምራትን እያደረገች ይገኛል፡፡
- ከሀንጻ ቤተክርስቲያኑ ግንባታ አንስቶ ንብረቷን ሊሰርቁ እሰከመጡት ሽፍቶች ድረስ ድንቅ ታአምራቷን እየገለጸች ዘመናት መሀል አልፋለች
- በታሪክ እየጠፉ ያለዉን የአንኮበር ወረብ ለትዉልድ በማቆየት ቦታዉን በሊቃዉንት ምስጋና እየከበረ እንዲቆይ ሆኗል በተለይም የመስከረም 10፣የዘመነ ጽጌ፣የህዳር 21፣የጥር 11 እና 21 ክብረ በአላት ልዩ የወረብ ጣእመ ዝማሬዎች የማይረሱ ናቸዉ፡፡
- በተለያዩ ነገስታት እና አንዲሁም ሊቃዉንት የተበረከቱ ቅርሶችን ፣የታሪክ መዛግብትን እና የዘመኑ የጥበብ አሻራ ያረፈባቸዉን የስዕል እና ኪነ ህንጻ ዉጤቶች ለትዉልድ በማቆየት እንዲሁም በሙዚዬም ለጎብኚዎች ክፍት በማድረግ ትዉልድን በመቅረጽ ሰፊ አገልግሎት እየተሰጠባት ይገኛል፡፡
- የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን እና ሊቃዉንቱን የሚያፈሩ የአብነት ትምህርት ቤቶችን ክፍት በማድረግ ተማሪዎች እንዲማሩ በማድረግ ሰፊ አገልግሎት እየተሰጠባት ያለች ታላቅ ስፍራ ናት::

7.3. <u>አዳዲ ማርያም</u>

- የአዳዲ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ሰባ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ፣ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት፣ በሌመን ወረዳ ውስጥ የምትገኝ እንደ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ከወጥ ድንጋይ ተፈልፍላ የተሠራች ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ናት። ቤተ ክርስቲያኒቱ በመቸ ዓመተ ምህረት እንደተሠራች እርግጠኛ መረጃ የለም። ሆኖም ግን በአጠቃላይ መልኩ በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ

ዘመን እንደተመሰረተች ይታመናል። ይኸውም ከላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ሥራ ፍጻሜ ቀጥሎ መሆኑ ነው።

- ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተመሰረተች ጀምሮ እስከ ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለአምልኮ ስታገለግልግል ቆይታ በኋላ በዚሁ ዘመን በተነሳው ግርግር ምክንያት ቤተ ክርስቲያኗን ለማትረፍ ሲባል በአፈር ተሞልታ በምድር ተቀበረች። ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በ፲፰፻፹፯ ዓ/ም ከተቀበረችበት እስካስወጧት ድረስ ቤተ ክርስቲያኒቱ በተቀበረችበት ተረስታ ቆየች። በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያኒቱ ከውሃና እጽዋት ጉዳት በስተቀር ብዙ ጥፋት ሳይደርስባት አሁን ድረስ ትገኛለች።
- አዳዲ ደብረ ምሕረት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥዕላት የላትም ነገር ግን እንደ ጥንቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሠራር የተለያዩ ጌጦች ነበራት። ቤተ ክርስቲያኗ ፲፱ ሜትር ተኩል እርዝመት ሲኖራት ፲፯ ሜትር ወርድና ፯ ሜትር ቁመት አላት። ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለመግባት ሦስት አይነት ደረጃዎች አሉ፡- ሁለቱ ለወንዶችና ቀሳውስት ሲያገለግሉ አንዱ ደግሞ ለሴቶች ያገለግላል። ጣሪያዋ በሳር የተሸፈነ ስለሆነ ከሩቅ ለማየት ያዳግታል፣ ቤተ ክርስቲያኗ ከከባት አለት በመካከል በተሠራ መተላለፊያ የተለየች ሲሆን ከባቢው አለት ውስጥ ተፈልፍለው የተሰሩ ቀዳዶች ለመጸለያና ለመጾሚያ ያገለግላሉ። ዋናዋ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ክፍል አላት፡ አንዱ ለቀሳውስት ሲሆን ሁለተኛው ድርሳኖችን ይይዛል። ምዕመናን እና ዘማሪዎች በነዚህ ክፍሎች ዙርያ ባለው በመተላለፊያው ይሰየማሉ።

7.4. ብርብር ማርያም

- ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር ስብከተ ወንጌል ከተዳረሰባቸው ጥቂት የዓለም ሀገራት መካካል አንደኛዋ ነበረች፡፡ አይደለም ስብከተ ወንጌል መሥዋዕተ ኦሪት ከተሠዋባቸው በጣም ጥቂት የእስራኤል እና የኢትዮጵያ ሥፍራዎች መካካል አንዱ ደቡቡ የሀገራችን ክፍል ነው፡፡ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ተዘንግቶ ወይም ተረስቶ የቀረ ሳይሆን በሰሜን አሞ የምትገኘው ብርብር ማርያም የዚህ በረከት ተካፋይ ናት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኸ በረከት ከደረሳቸው አምስት ስፍራዎች መካከል ብርብር ማርያም ትጠቀሳለች፡፡ ይኸም ደቡቡ እንዴት ዓይነት የአውነተኛዋ

ሃይማኖት መናኸሪያ እንደነበር መረዳት አይከብድም፡፡ አይደለም በኢትዮጵያ በሀገረ እስራኤልም ቢኾን መሥዋዕተ ኦሪት የተሠዋባቸው ቦታዎች ጥቂቶች ናቸውና፡፡ ከእነዚህ መደመር ደግሞ ምን ዓይነት ጸጋ እና በረከት መታደል እንደኾነ እናውቃለን፡፡

- ብርብር ማርያም የምትጠቀሰው በማዕከልነቷ መኾኑን ስናስብ ዙሪያዋን የምትወክል እንደኾነች እንረዳለን፡፡ በዘመነ ብሉይ እንዲህ የሚያበራ በረከት ይታፈስባት የነበረችው አካባቢ በእነ አጼ ገብረመስቀል፣ በእነ ቅዱስ ያሬድ እና አቡነ አረጋዊ ዘመንም እነዲሁ ከፍ እንዳለች እና እንደ ደመቀች መቀጠሏ ይነገራል፡፡ ንጉሡ አጼ ገብረመስቀል የብርብር ማርያምን ዜና ሰምተው ይህችንስ ልሳለማት በማለት ከአክሱም ተነሥተው ጻድቁ አቡነ አረጋዊን ይዘው ሠራዊት አስከትለው ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ አቋርጠው ብርብር ማርያምን ተሳልመዋታል፡፡ ታቦተ ማርያምን አስገብተው ክርስትናን አስፋፍተው ተመልሰዋል፡፡ ይኸ የኾነው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡
- ውለ አድሮም የአቡነ ተክለሃይማኖት ደቀመዛሙርት በየአቅጣጫው እየተዘዋወሩ ሲያስተምሩ ከዳሰሱት አካባቢ መካከል ደቡቡ የሚጠቀስ ክልል ነው፡፡ እንዲያውም ራሳቸው አቡነ ተክለሃይማኖት ሞቶለሚ ከተባለው የዳሞት ንጉሥ ጋር ያደረጉት ተጋድሎ በዚያው አካባቢ የኾነ ነው፡፡ ነገር ግን ያ ሁሉ ድካም የተደከመበትን ስፍራ ግራኝ የተባለ እኩይ ተነሥቶ ብዙውን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን በሺህ ዓመታት ወደኋላ የመለሰ ጥፋት አጠፋ፡፡ በየስፍራው ተተክለው የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት አፈራረሰ፡፡ መጻሕፍቱን አቃጠለ፣ ካህናቱን እና ምእመናኑን የቻለውን ገደለ፡፡ ለዚህ ቋሚ ምስክር ይኾን ዘንድ ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት ቦረዳ እየተባለ በሚጠራው የሰሜን ኦሞ ክልል ውስጥ በዋሻ ውስጥ ተቀብረው የተገኙት ታቦታት እና በተደጋጋሚ የተፈጸሙት ገቢራተ ተአምራትን እግዚአብሔር አሳየን፡፡ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ቤተክርስቲያን ደቡቡን የሀገራችን ክፍል የተወችበት በታሪክ የሚጠቀስ ዘመን የለም፡፡
- ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ በልዩ ሁኔታ በእግዚአብሔር ሀገርነት ተጽፎ የሚገኘው የደቡቡ የሀገራችን ክፍል አቡነ ተክለሃይማኖትን የመሰለ ደገኛ ፓትሪያርክ ያወጣ ነው፡፡ ከእርሳቸው ወዲህ እንደእርሳቸው ያለ የሚመስላቸውም እስካሁን አላየንም፡፡ በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ደከም ብሎ የነበረው የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ አሁን በተለየ

ተአምራዊ ሁኔታ ከፍ ወዳለ ደረጃ እየመጣ ይገኛል፡፡ ሰምቶም አድንቆም ዝም የማይሉት ተአምራት፡፡ ተናግረው የማያስረዱት የመንፈስቅዱስ እሳት በደቡብ ኦሞ ተቀጣጥሏል፡፡

ዋቢ መጻሕፍት

1. ቅዱሳት መካናት በኢትዮጵያ
2. ስንክሳር
3. መዝገበ ታሪክ